https://www.path-2-happiness.com/am

الطريق إلى السعادة
The Path to Happiness



# የደስተኛነት መንገድ

## ማውጫ

**የደስተኛነት መንገድ**

የደስተኝነት ጽንሰ ሐሳብና ትክክለኛ ምንነቱ

ደስተኝነት ከእርካታ የተለየ ነው፡

ፈጽሞ. . ደስተኝነት እረፍት ውስጥ አይገኝም!!

የደስተኝነት መንገድ . . የሰው ልጅ ከራሱ፣ከሕይወትና ከፍጥረተ ዓለሙም ጋር የሚያደርገው እርቅ ነው፡

የደስተኝነት መንገድ ጠቋሚ ምልክት፡

በቅርቢቱ ሕይወት ለደስተኝነት የሚያበቁ መረማመጃዎች በእስላም፡

ከደስተኝነት መንገድ የመራቅ ስቃይና ዕድለ ቢስነት፡

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

# የደስተኛነት መንገድ

## የደስተኝነት ጽንሰ ሐሳብና ትክክለኛ ምንነቱ

መታደል ወይም ደስተኝነት በሚለው ቃል ምንነት ላይ በሰዎች መካከል ልዩነት ይታያል:: አንዳንዶቹ ከእርካታ፣ከምቾት፣ወይም ከገንዘብ፣ከሥልጣንና ከዝና . . ጋር የተቆራኘ አድርገው ይመለከቱታል:: ለዚህም ሲሉ ብዙ ሰዎች በተለያዩ መንገዶች ደስተኝነትንና መታደልን በመፍለግ ሕይወታቸውን ያሳልፋሉ:: እርግጥ ነው . . ደስተኝነት ወይም መታደል ውስጣዊ እርካታ፣ምቾት፣መረጋጋትና ሕሊናዊ እፎይታ ሲሰማ ከውስጥ የሚመነጭ ስሜት ነው:: ይሁን እንጂ ሰዎች ስለ ደስተኝነት ያላቸው አመለካከት እንደ ባሕርያቸውና እንደ ዝንባሌያቸው፣እንደ ትልማቸውና እንደ ምኞቶቻቸው፣ሌላው ቀርቶ እንደ ማሕበረሰባዊ ልዩነቶቻቸውም መለያየት የተለያየ ነው:: አንዳንዶቹ ደስተኝነትን በገንዘብና በሀብት፣በተንደላቀቀ ቤትና ኑሮ፣በክብርና በሥልጣን ውስጥ ሲመለከቱት፤ሌለሎቹ ደግሞ በጥሩ ሚስት ወይም ባል፣በልጆችና መልካም ቤተሰብ፣በሥራ ወይም በትምሕርት ደረጃ ውስጥ ያዩታል:: ምናልባትም ደስተኝነትን ከሚወዱት ጋር በመገናኘት ወይም ከሚጠሉት በመገላገል፣ከዓለማዊ ደስታ ርቀው የምናኔ ሕይወት በመምራት፣ወይም ድሆችና ችግረኞችን በመርዳት ውስጥ የሚመለከቱም ይኖራሉ:: በጣም አስገራሚው ግን ከነዚህ አንዳቸውን በእውነትና በእርግጠኝነት አንተ ደስተኛ ነህ ወይ? ብለን ስንጠይቅ መልሱ



### የደስተኝነትና የእርካታ ሃይማኖት

‹‹እንዲህ ስል ራሴን እጠይቅ ነበር፦ ሙስሊሞች ድሆችና ኋላ ቀሮች ሆነው ሳለ ሕይወታቸውን ሞልቶ የሚያጥለቀልቅ ደስተኝነት የሚሰማቸው ለምንድን ነው?! ስዊድናውያን የተንደላቀቀ የብልጽግና ሕይወት እየመሩ በጭንቀትና በውጥረት የሚሰቃዩት ለምንድነው?! አገሬ ስዊዘርላንድ ጭምር የበለጸገችና የተንደላቀቀ የኑሮ ደረጃ ላይ የምትገኝ እየሆነች እዚህም ስዊድን ውስጥ የተሰማኝ ስሜት ነው የሚሰማኝ!! ከዚህ ሁሉ በመነሳትም የምሥራቅ ሃይማኖቶችን ማጥናት እንደሚያስፈልገኝ ተረዳሁና በሕንዱ ሃይማኖት ጥናቴን ጀመርኩ:: ብዙ አላሳመነኝም:: የእስላምን ሃይማኖት ማጥናት ጀመርኩ:: ከሌሎች ሃይማኖቶች ጋር ቅራኔ የሌለው ብቻ ሳይሆን የሃይማኖቶች መደምደሚያ ሆኖ ለሁሉም ቦታ የሚሰጥ መሆኑ ሳበኝ:: ይህ ከንባቤ ስፋት ጋር መስፋት ጀምሮ ሙለ በሙሉ አእምሮዬ ውስጥ እስከ መስረጽ የደረሰው እውነታ ነው::››


**ሮዤህ ዶባኬይ**
**ስዊዘርላንዳዊ አሳቢና ጋዜጠኛ**



### የሰው ልጆች መታደል

‹‹ዘመናዊው የምዕራብ ሥልጣኔ ነፍስን ማርካት የተሳነውና ለሰው ልጆች ደስተኝነትን ማጎናጸፍ ያቃተው መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል:: በዚህ ውድቀቱ ምክንያትም ሰውን ወደ እድለ ቢስነትና ወደ ውጥረት መቀመቅ እንዲዘቅጥ አድርጎታል:: የዘመናዊው ሳይንስ ጥረቶችም ወደ ውድመትና ጥፋት ያነጣጠሩ በመሆናቸው፣ሳይንስም በዚህ ሁኔታ በምሉእነት ከመገለጽ፣ወይም በዘመነ እስላም እንደ ነበረው የሰብአዊ ፍጡራን መገልገያ መሣሪያ ከመሆን የራቀ ነው::››

**ነሲም ሱሳህ**
**ዒራቃዊ ይሁዲ የሆነ ሌክቸረር**



አሉታዊ መሆኑ ነው!!

ስለዚህም ለደስተኝነት የሚሰጠው ትርጓሜ እንደየሰውና እንደየሕብረተሰቡ የሚለያይ መሆኑን እንረዳለን:: ለዚህም ይመስላል አንዳንድ ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶች ‹‹የሕዝቦች የደስተኝነት መሰላል›› የተሰኘ መለኪያ በማስቀመጥና የተለያዩ መጣኞችን በመተንተን ለመሰላሉ ደረጃዎችን መድበው የትኞቹ ሕዝቦች ይበልጥ ደስተኞች እንደሆኑ ለማወቅ የፈለጉት:: ውጤቱ ግን ለሁሉም ያልተጠበቀ ዱብ እዳ ነበር የሆነው:: ሁላችንም እንደምናውቀው እያንዳንዱ አሜሪካዊ ከሚመራው ከፍተኛ የብልጽግና ሕይወት ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ፣በመመዘኛው መሰረት ያሽቆለቆለ ነጥብ ያገኘው የዩ.ኤስ. አሜሪካ ሕዝብ ከሁሉም በላይ ደስተኛ ሳይሆን፣ከሁሉም ይበልጥ ደስተኝነት የራቀው ሆኖ ነበር የተገኘው:: በጣም አስደናቂው ሆኖ የተስተዋለው በከባድ ድህነት ውስጥ ኑሮውን የሚገፋው የናይጄሪያ ሕዝብ ከዓለም ሕዝቦች ሁሉ ከፍተኛውን የደስተኝነት ነጥብ ያስመዘገበ፣ከሁሉም ይበልጥ ደስተኛ ሕዝብ ሆኖ መገኘቱ ነው!!

ይህ የአሜሪካው ኒውዝዊክ መጽሔት የዓለማችን ይበልጥ ደስተኛው ሕዝብ የትኛው እንደሆነ ለማወቅ ያደረገው ዳሰሳ ውጤት ሲሆን፣በአብላጫው ሙስሊም የሆነው ደሃው የናይጄሪያ ሕዝብ ጥናቱ ውስጥ ከተካተቱ ስልሳ አምስት አገሮች ውስጥ በደስተኝነት የአንደኝነቱን ቦታ ይዟል:: ቀጣዮቹን ደረጃዎች ሜክሲኮ፣ቬንዙዌላና ሰልቫዶር ሲይዙ፤የበለጸጉ አገሮች ግን - ዘገባ አቅራቢውን ባስደመመ ሁኔታ- በደስተኝነት መሰላሉ ዝቅተኛ ደረጃዎችን ይዘዋል:: እዚህ ላይ ጥናቱ ያካተታቸው አብዛኞቹ አሜሪካውያን ደስተኝነት ከሀብትና ከገንዘብ[1] ጋር የማይገናኝ መሆኑን አምነው የተቀበሉ መሆናቸውን ቆም ብለን ማየት ያስፈልግ ይሆናል:: ይህ ተጣጣፊ በሆነና ከሁሉም ይበልጥ ተስፈንጣሪ በሆነ የካፒታሊዝም ዓይነት ላይ በተመሰረተ ሕብረተሰብ ውስጥ ያልተለመደ እንግዳ ነገር መስሎ ይታያል:: አሜሪካ ውስጥ[2] እየተስተዋለ ያለውን የሃይማኖትን ዳግም

(1) ኒውዝዊክ መጽሔት፣የዐረብኛው እትም፣3/4/2004፣ገጽ 58


(2) ኒውዝዊክ መጽሔት፣የዐረብኛው እትም፣6/9/2004

https://www.path-2-happiness.com/am

ተመልሶ መስፋፋት ክስተትን እንዲዳስስ ጓላ ላይ መጽሔቱን የገፋፋውም ይኸው ጉዳይ ነው። በዚህም አሜሪካውያን ደስተኝነትን ለማግኘት ሲሉ ለታከታዮቻቸው ነፍሶች ማከሚያነት በሚወሰዱት ጊዜያዊ ትኩረትን የማሰባሰብና የአስተውሎት ሕክምና አማካይነት ስለሚያደርጉት ብርቱ ጥረት ጥያቄዎች መነሳት ጀምረዋል።

ምናልባትም ስለ ደስተኝነት ምንነትና እንዴትስ ማገኘት እንደሚቻል ትርጓሜና ትንተና በሰጡት ብዙዎቹ ዘንድም ይህንኑ ችግር እናስተውላለን። በአፍላጦን አመለካከት ደስተኝነት የሰብእና ትሩፋቶች (ጥበብ፣ጀግንነት፣ቁጡብነትና ፍትሕ) ናቸው። በርሱ እምነት የሰው ልጅ ምሉእ የሆነ ደስተኝነት የሚያገኘው ነፍሱ ወደ ሌላኛው ዓለም ስትመለስ ብቻ ነው። አርስቶትል ደግሞ ደስተኝነትን ከአላህ የሚለገስ ችሮታ አድርጎ የሚመለከት ሲሆን፣አምስት ገጽታዎች አሉት ይላል። እነሱም፦ የአካልና የስሜት ሕዋሳት ደህንነት፣ሀብትን ማግኘትና በአግባቡ መጠቀም፣በሥራ ስኬታማ መሆንና ዓለማን እውን ማድረግ፣የአእምሮ ጤንነትና ትክክለኛ እምነት፣መልካም ዝና እና በሰዎች ዘንድ ተቀባይነትን ማትረፍ ናቸው። በስነልቦና ሳይንስ ደስተኝነትን የኑሮ ስኬት ደረጃ ነጽብራቅ ወይም የአስደሳች ነገሮች ሁነቶች ድግግሞሽ አማካይ ነጸብራቅ[(1)] አድርጎ መረዳት ይቻላል። ይሁን እንጂ በደስተኝነት ጽንሰ ሐሳብ ግንዛቤ ዙሪያ ያለው ይህ ልዩነት ‹‹ደስተኝነት ምንድነው? እንዴትስ ደስተኛ መሆን እችላለሁ? ደስተኝነት እርካታን በማግኘት ብቻ እውን ሊሆን ይችላል?›› የሚሉ ጥያቄዎች በጥያቄነት እንዲቀጥሉ ያደርጋል።

(1) የደስተኝነት ስነልቦና፣ማይክል አርጃይል፣ፊይሰል ዐብዱልቃድር ወደ ዐረብኛ እንደተረጎመው





## ደስተኝነት ከእርካታ የተለየ ነው፦

ሰው ብዙ ጊዜ የተለያዩ እርካታዎችን ፍለጋ ይባዝናል፤በለስ ቀንቶት ያገኘውን እርካታ ከማጣጣም አያመነታም። አርኪ ነገሮችን ሁሉ ቢያገኝ ደስተኝነትን አገኛለሁ ብሎ ይገምታል። ግና ከደስተኝነት ከማንም ይበልጥ ሩቅ መሆኑን በድንገት ይገነዘባል። ቁሳዊ እርካታዎች በዓይነት የተለያዩና በቅርጽና ይዘታቸውም ተለዋዋጮች ናቸው። ይሁን እንጂ ሁሉም እርካታና ሁሉም አርኪ ነገር ደስተኝነትን አያጎናጽፍም። በዚህ ምክንያት ነው በደስተኝነት ጽንሰ ሐሳብና በእርካታ ጽንሰ ሐሳብ መካከል መምታታት የሚፈጠረው። ትክክለኛው ግንዛቤ ሁለቱ በአንድ በኩል ሲገናኙ በሌላ በኩል ደግሞ የሚለያዩ መሆናቸው ነው። አንድነታቸው ሁለቱም እርካታን የሚሰጡ ከመሆናቸው አንጻር ነው። የሚለያዩት ደግሞ እርካታ ወዲያው መጥቶ መንስኤው ከሄደ በኋላ ወዲያውኑ አብሮት የሚጠፋ ብቻ ሳይሆን ቁጭትና ብርቱ ጸጸትን ትቶ ሊያለፍ የሚችል በመሆኑ ሲሆን፣ደስተኝነት ግን ለረዥም ጊዜ አብሮ የሚቆይ ከመሆኑ አንጻር ነው።

በእርካታና በደስተኝነት ግንዛቤዎች መካከል ያለው ይህ የመደበላለቅ ሁኔታ፣አንዳንድ ጊዜ ከራሱ ከግለሰቡ በኩል የሚመጣ ሲሆን፣ሁሉንም እርካታዎች ደስተኝነት አድርጎ የመመልከት አዝማሚያን ያሳያል። ዝነኛ መሆን በሰው ዘንድ ታዋቂ መሆንን፣ቅድሚያ ማግኘትንና ተቀባይነትን . . ስለሚያስገኝ ወደር የሌለው እርካታ ይሰጣል። ይህ ሁሉ የእርካታ ዓይነት ነው። ይሁን እንጂ ዝና እና ታዋቂነት፣ሀብትና ሥልጣንም ኖሮት ይህን ሁሉ ይዞ በጭንቀትና በውጥረት እየተሰቃየ ደስተኝነትን የተነፈገና ስነልቦና ሐኪሞች ዘንድ ለሕክምና የሚመላለስ፣ወይም ከጭንቀቱ ለመገላገል ሲል ራሱን በመግደል ሕይወቱን የቋጨ ሰው ቁጥሩ እጅግ ብዙ ነው!! ስንቶቹ ታዋቂና ዝነኛ ግለሰቦች ከጭንቀት ለመገላገል ሲሉ ራስን ማጥፋት እንደ መፍትሔ እንደወሰዱ ሁላችንም እናውቃለን!! ብዙዎች ደስታን ፍለጋ ከልክ ባለፈ ሥጋዊ ፍላጎት ውስጥ ተዘፍቀው በዝሙት የሚጠመዱ ሲሆን፣ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን የኤድስ ሰለባ ሆነው መቀጠፋቸውን እንሰማለን!! ሕገወጥ ወሲብ ጊዜያዊ እርካታ ሊሰጥ ይችል ይሆናል፤ግና በቋሚነት ቤተሰብን ያፈርሳል፣ለሕብረተሰቡም ጠንቅ ይሆናል። ወሲብ ነክ ፊልም አንድ ዓይነት ጊዜያዊ እርካታን ይሰጥ ይሆናል፤ግና የግለሰቡን ሰብእና ያወድማል፣የተቀደሰውን ትዳራዊ ትስስር ያናጋል፤የማሕበረሰቡን ደህንነትም አደጋ ላይ ይጥላል። ከሌሎች ፍላጎቶችና እርካታዎች ምግብ አንዱ ሲሆን፣ከመጠን ያለፈ የምግብ ፍላጎትም የሐኪሞችና የጤና ተቋማት ቋሚ እንግዳ መሆንን ያስከትላል!!

በሁለቱ ጽንሰ ሐሳቦች መካከል ያለው መምታታት አንዳንዴ ከተወሰኑ ወገኖች በኩል ሆን ተብሎ የሚደረግ ሲሆን፣ብዙዎች የተለያዩ የፍላጎት ማርኪያዎችን ደስተኝነትና የእውነተኛ ደስታ ምጭ እንደሆኑ አድርገው ለማሻሻጥ ሲጥሩ ይስተዋላሉ። ዓላማቸውም የሰውን ትኩረት በመቆጣጠር ወደ ተለያዩ

https://www.path-2-happiness.com/am

አቅጣጫዎች መውሰድ ነው:: እጽ ተጠቃሚ ወጣት መጀመሪያ ላይ መጠቀም የሚጀምረው ለጊዜያዊ እርካታው ሲሆን፣በኋላ ግን እጹን የሚያቀርብለት ሰው እንዳሻው የሚጫወትበት አሻንጉሊት ወደ መሆን ይሸጋገራል!

የተለያዩ ሸቀጦችን ለማሻሸጥ የሚቀርቡ ማስታወቂያዎችም የሰዎችን ትኩረት ስበው አእምሮን ስለሚቆጣጠሩ ሸማቹን ያደናግራሉ::

እናም ደስተኝነት አንድ ሰው የሚፈልገውን ሁሉ በማግኘቱ የሚደረስበት ነገር አይደለም ማለት ነው:: እንዲህ ቢሆን ኖሮ የናጠጡ ሀብታሞችና መሪዎች ከሰው ሁሉ በላይ ደስተኞች በሆኑ ነበር:: ሳይንሳዊ ጥናቶችና ተግባራዊ አስተውሎዎች ግን ይህንን ያስተባብላሉ:: ምናባትም እንዲህ መሆኑ አላህ (ሱ.ወ.) በዚህ ዩኒቨርስ ውስጥ ያኖረው ምሉእ ፍትሑ አንዱ መገለጫ ሊሆን ይችላል:: ብዙ ድሆችና ችግረኞች ደስተኞች መሆናቸውን መመልከት ይቻል የለም! ብዙ የተንደላቀቁ ሀብታሞች እነርሱ ዘንድ በሌሉና ድሆች ዘንድ በሚገኙ ብዙ ሕሊናዊ እርካታዎች ይቀኑ የለም!! ደስተኝነት ምናልባት በእረፍት ውስጥ ይገኝ ይሆን?! እስኪ እንመልከት::



## ፈጽሞ. . ደስተኝነት እረፍት ውስጥ አይገኝም!!

ብዙ ሰዎች እረፍት ማለት ደስተኝነት ነው ብለው ስለሚገምቱ እረፍት ለማግኘት ይጥራሉ:: እረፍት ግን ለጭንቀት፣ለሀሳብ፣ለድብርትና ለብቸኝነት ሊዳርግ ይችላል:: ሰው ብዙ ጊዜ አካሉን እያደከመም ደስተኝነት የሚሰማው መሆኑንና አልፎ አልፎም ድካምና ችግር ራሱ ደስታና እርካታ የሚሆንበት ሁኔታ መኖሩን ይረሳል:: ውሃ ጉድጓድ ውስጥ የወደቀ ሕጻን ሕይወት ለማትረፍ ራሱን ወደ ጉድጓዱ ለመወርወር የተገደደ ሰው ሊደርስበት የሚችለው የአካል ጉዳትና ስብራት፣የሚያስከትለው ሕመምና ስቃይ እንዳለ ሆኖ የሕጻኑን ሕይወት ለማትረፍ በመቻሉ ብቻ ደስተኝነት ይሰማዋል:: ምሁራንና ተመራማሪዎች በጥናትና ምርምራቸው ላይ የሚገጥማቸው ችግር፣ድካምና ልፋት ከባድ ቢሆንም ወደ ከፍተኛ ደረጃ የሚያደርሳቸው በመሆኑ ልፋቱ ደስታና እርካታን ይሰጣቸው የለም?!! እስፖርተኛም እንዲሁ ላቡን እያንጠፈጠፈና ከከባድ ድካም ጋር እየታገለ ደስተኝነት ይሰማዋል:: ድሆችንና ችግረኞችን ለመርዳት የተሰማራ በጎ አድራጊም ከድካሙና ከልፋቱ ጋር በሚሰጠው አገልግሎት ተደሳች ይሆናል:: የሚወደውን ገንዘብና ንብረት ሌሎችን ለመርዳት ሲል የሚለግስ፣ጊዜውን፣ዕረፍቱንና የሚወደውን ነገር የሚሰዋ ሰውም ሕሊናዊ እርካታና ደስተኝነትን ያገኛል::

በዚህ የመጠለለፍ ሁኔታና ለደስተኝነት በሚሰጡ የተለያዩ ትርጓሜዎች ምክንያት፣የደስተኝነትን ምንነትና እውነተኛውን መታደል እንዴት ማግኘት እንደሚቻል ለማወቅ ያላሰለሰ ጥረት የሚያደርግ ሰው ግን ግራ መጋባቱን ይቀጥላል::

### መኖር የሚቻል አልሆነም!!

‹‹ራሷን ከመግደሏ በፊት የመጨረሻ ማስታወሻዋን ፦ ‹ሕይወት ሊኖሩት የሚቻል አልሆነም!! ይቅርታ አድርጉልኝ::› ብላ አሰፈረች::

ዳሊዳ

ዓለም አቀፍ ታዋቂነትን ያገኘች ዘፋኝ

## 1- የሰው ልጅ

### ከምን ተፈጠረ?!

አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፡-

{هُوَ ٱلَّذِى خَلَقَكُم مِّن تُرَابٍ ثُمَّ مِن نُّطْفَةٍ ثُمَّ مِنْ عَلَقَةٍ ثُمَّ يُخْرِجُكُمْ طِفْلًا ثُمَّ لِتَبْلُغُوٓاْ أَشُدَّكُمْ ثُمَّ لِتَكُونُواْ شُيُوخًا وَمِنكُم مَّن يُتَوَفَّىٰ مِن قَبْلُ وَلِتَبْلُغُوٓاْ أَجَلًا مُّسَمًّى وَلَعَلَّكُمْ تَعْقِلُونَ ﴿٦٧﴾} [غافر: ٦٧]

‹‹እርሱ ያ ከዐፈር፣ከዚያም ከፍትወት ጠብታ፣ከዚያም ከረጋ ደም፣የፈጠራችሁ ነው:: ከዚያም ሕጻናት አድርጎ ያወጣችኋል፤ከዚያም ጥንካሬያችሁን ትደርሱ ዘንድ፤ከዚም ሽማግሌዎች ትኾኑ ዘንድ፣(ያቆያችኋል)፤ከናንተም ውስጥ ከዚህ በፊት የሚሞት አለ፤(ይህንንም ያደረገው ልትኖሩና) የተወሰነ ጊዜንም ልትደርሱ፣ታውቁም ዘንድ ነው:: ››[አል ሙእሚን፡67]

አዎ . . የተፈጠረው ከአፈርና ከጠብታ ውሃ ሲሆን መጨረሻው በድን ሬሳ መሆን ነው:: በውስጡ ቆሻሻ ተሸክሞ ይሄዳል፤ከአካላቱ የሚወጡ ነገሮችን ሁሉ ይጸየፋል:: ከዚህ ሁሉ በኋላ ግን ፈጣሪ ጌታውን ተሚጋች ይሆናል፤ሰው ከሓዲነቱም ከፉ!! አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፡-

{قُتِلَ ٱلْإِنسَٰنُ مَآ أَكْفَرَهُۥ ﴿١٧﴾ مِنْ أَىِّ شَىْءٍ خَلَقَهُۥ ﴿١٨﴾ مِن نُّطْفَةٍ خَلَقَهُۥ فَقَدَّرَهُۥ ﴿١٩﴾ ثُمَّ ٱلسَّبِيلَ يَسَّرَهُۥ ﴿٢٠﴾ ثُمَّ أَمَاتَهُۥ فَأَقْبَرَهُۥ ﴿٢١﴾ ثُمَّ إِذَا شَآءَ أَنشَرَهُۥ ﴿٢٢﴾}[عبس: ١٧- ٢٢]

‹‹ሰው ተረገመ፤ምን ከሓዲ አደረገው? (ጌታው) ከምን ነገር ፈጠረው? (አያስብምን?) ከፍትወት ጠብታ ፈጠረው፤መጠነውም:: ከዚያም (መውጫ) መንገዱን አገራው:: ከዚያም ገደለው፤እንዲቀበርም አደረገው:: ከዚያም (ማንሳቱን) በሻ ጊዜ ያስነሳዋል::››[ዐበሰ፡17-22]

ከዚህ ሁሉ ጋር ግን ከተቀሩት ፍጥረታት ሁሉ ክቡር ፍጡር ተደርጓል:: አላህ (ሱ.ወ.) መላእኮችን ለአባቱ ለኣደም እንዲሰግዱ አዟል:: ምድሪቱና እንስሳትን ለርሱ አገልግሎት የተገሩ እንዲሆኑ ተደርገዋል:: ተአምር መስራት የሚችል አእምሮም ለግሶታል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፡-

{وَلَقَدْ كَرَّمْنَا بَنِىٓ ءَادَمَ وَحَمَلْنَٰهُمْ فِى ٱلْبَرِّ وَٱلْبَحْرِ وَرَزَقْنَٰهُم مِّنَ ٱلطَّيِّبَٰتِ وَفَضَّلْنَٰهُمْ عَلَىٰ كَثِيرٍ مِّمَّنْ خَلَقْنَا تَفْضِيلًا ﴿٧٠﴾}[الإسراء: ٧٠]

‹‹የኣደምንም ልጆች በእርግጥ (ከሌላው ፍጡር) አከበርናቸው፤በየብስና በባሕርም አሳፈርናቸው፤ከመልካሞችም (ሲሳዮች ሰጠናቸው)፤ከፈጠርናቸውም ፍጡሮች በብዙዎቹ ላይ ማብለጥን አበለጥናቸው::››[አል እስራእ፡70]

እናም የሰውን ልጅ ስረ መሠረት መረዳት የሚቻለው እነዚህን ሁለት እውነታዎች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው:: በዚህ ግንዛቤ



መሰረትም የሰው ልጅ የሚያስመዘግበው ድል፣ክብር፣ዕድገት፣ሀብት፣ዕውቀትና ሌላውም ስኬት አላህ (ሱ.ወ.) ከቸረው ጸጋ ብቻ የተገኘ መሆኑን በማመን ላይ የሚመሰረተው ምዘና ትክክለኛው ምዘና ይሆናል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፡-

{وَمَا بِكُم مِّن نِّعْمَةٍ فَمِنَ ٱللَّهِ ۖ ثُمَّ إِذَا مَسَّكُمُ ٱلضُّرُّ فَإِلَيْهِ تَجْـَٔرُونَ ﴿٥٣﴾}[النحل: ٥٣]

‹‹ማንኛውም በናንተ ላይ ያለው ጸጋ ከአላህ ነው፤ከዚያም ችግር በደረሰባችሁ ጊዜ፣ወደርሱ ብቻ ትጮኻላችሁ::››[አል ነሕል፡53]

የሰው ልጅ በራሱ የሥጋና የአጥንት ክምር እንጂ ሌላ ምንም አይደለም:: ምጥቀቱ የሚመጣው በጠቃሚ ዕውቀትና በመልካም ሥራ የማነጽና የማሰልጠን ግዴታ ባለበት ነፍሱ በኩል ነው:: ሰው ደካማና አቅም የለሽ ከመሆኑም ጋር አላህ (ሱ.ወ.) ግን ለተቀሩት ሌሎች ፍጥረታት አቅርቦ መሸከም ያልቻሉትን አማና (ኃላፊነት) መቀበልና መሸከም የሚያስችሉ ባሕርያትን አጎናጽፎታል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፡-

{إِنَّا عَرَضْنَا ٱلْأَمَانَةَ عَلَى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَٱلْجِبَالِ فَأَبَيْنَ أَن يَحْمِلْنَهَا وَأَشْفَقْنَ مِنْهَا وَحَمَلَهَا ٱلْإِنسَٰنُ ۖ إِنَّهُۥ كَانَ ظَلُومًا جَهُولًا ﴿٧٢﴾}[الأحزاب: ٧٢]

‹‹እኛ አደራን በሰማያትና በምድር፣በተራራዎችም ላይ አቀረብናት፤መሸከሟንም እንቢ አሉ፤ከርሷም ፈሩ፤ሰውም ተሸከማት፤እርሱ በጣም በደለኛ ተሳሳች ነውና::››[አል አሕዛብ፡72]

የሰው ልጅ በእምነቱ እነዚህን ሁለት እውነታዎች የማመጣጠንና የማመዛዘን መስፈርት ካጓደለ፣ትኩረቱ በሙሉ ወደ መጀመሪያው እውነታ ብቻ ይሆንና ራሱን እንደ እንስሳት ሆዱንና ሥጋዊ ፍላጎቶቹን ብቻ ከማርካት ያለፈ ሌላ ዓለማ የሌለው ፍጡር አድርጎ በመውሰድ ሰብእናውን ያዋርዳል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፡-

{وَٱلَّذِينَ كَفَرُواْ يَتَمَتَّعُونَ وَيَأْكُلُونَ كَمَا تَأْكُلُ ٱلْأَنْعَٰمُ




### አጥጋቢ ምላሽ

‹‹የእስላም ሃይማኖት ትምሕርቶችን በመተግበር ለሰው ልጅ ሰብአዊ ተፈጥሮውና እውነተኛ ሰውኛ ሰብእናው ይገለጥለታል:: ራሱንና ማንነቱንም ያውቃል:: እስላም ግራ ላጋቡኝ ጥያቄዎቼ ምላሽ የሰጠኝ ብቸኛው ሃይማኖት ነው::››

**ሮዝማሪ ሃው**

**እንግሊዛዊት ጋዜጠኛ**



### እምቅ አቅምህን እወቅ

‹‹በሰዎች ግምት ደረጃው አነስተኛ ሥራዎቹም ጥቂት ቢሆኑ እንኳ፣እርሱ ግን ራሱን አገኘ:: ኤዲሰን ከትምሕርት ቤት የተባረረ ቢሆንም በፈለሰፋቸው ግኝቶቹ ውስጥ ራሱን አገኘ:: ለሰው ልጆች የዋለው ውለታም እጅግ የላቀ ነበር:: እናም ደስተኛ ለመሆን ቦታህን፣ሚናህንና አቅምህን ለማወቅ ዋናው ነገር ከራስህ ጋር መታረቅ ነው::››

**ኤዲሶሰን**





https://www.path-2-happiness.com/am

{وَٱلنَّارُ مَثۡوًى لَّهُمۡ ﴿١٢﴾}[محمد: ١٢]

‹‹እነዚያም የካዱት፣(በቅርቢቱ ዓለም) ይጣቀማሉ፤እንስሳዎች እንደሚበሉ ይበላሉ፤እሳትም ለነርሱ መኖሪያቸው ናት፡፡››[ሙሐመድ፡12]

ወይ ደግሞ ሁለተኛው እውነታ አእምሮውን አሸንፎ ወደ መኩራራት ወደ እብሪትና ልኩን ወደ ማለፍ ይወስደውና ወደ ፈጣሪ ጌታው ተመላሽ መሆኑን ያዘናገዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{كَلَّآ إِنَّ ٱلۡإِنسَٰنَ لَيَطۡغَىٰٓ ﴿٦﴾ أَن رَّءَاهُ ٱسۡتَغۡنَىٰٓ ﴿٧﴾ إِنَّ إِلَىٰ رَبِّكَ ٱلرُّجۡعَىٰٓ ﴿٨﴾}[العلق: ٦ـ ٨]

‹‹በውነቱ ሰው ወሰንን ያልፋል፤ራሱን የተብቃቃ (ባለ ሀብት) ኾኖ ለማየቱ፡፡ መመለሻው ወደ ጌታህ ብቻ ነው፡፡››[አል ዐለቅ፡6-8]

ስለዚህም የሰው ልጅ የራሱን ደረጃ አውቆ ከራሱ ጋር መታረቅ ይኖርበታል፡፡ በዚህ የተነሳ ከሰው ልጅ የደስተኝነት እጦት ዋነኛ ምክንያቶች አንዱ ራሱን አለማግኘቱና በሕብረተሰቡ ውስጥ ቦታው የት እንደሆነ አለማወቁ ነው፡፡ በመሆኑም ማንነቱን፣ሚናውን ስፍራውንና ምን ማበርከት እንደሚችል አያውቅም፡፡

## ለምን ዓላማ ተፈጠረ?!

አላህ (ሱ.ወ.) ፍጥረታትን ሁሉ ፈጥሯል፡፡ የፈጠራቸውም ፈጽሞ እንዲሁ ለከንቱ አይደለም፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{أَفَحَسِبۡتُمۡ أَنَّمَا خَلَقۡنَٰكُمۡ عَبَثٗا وَأَنَّكُمۡ إِلَيۡنَا لَا تُرۡجَعُونَ ﴿١١٥﴾ فَتَعَٰلَى ٱللَّهُ ٱلۡمَلِكُ ٱلۡحَقُّۖ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ رَبُّ ٱلۡعَرۡشِ ٱلۡكَرِيمِ ﴿١١٦﴾}[المؤمنون: ١١٥ـ ١١٦]

‹‹የፈጠርናችሁ ለከንቱ መኾኑን እናንተም ወደኛ የማትመለሱ መኾናችሁን ጠረጠራችሁን? (ለከንቱ የፈጠርናችሁ መሰላችሁን?)፡፡››[አል ሙእምኑን፡24]

የፈጠራቸው፣በጸሎት ስነ ሥርዓቶች ብቻ ሳይወሰን፤የሰውን ሥራ፣ጨዋታውንና ቀልዱን ሳይቀር ሙሉ ሕይወቱን በሚሸፍነው፣ በተሟላው አጠቃላይ የአምልኮተ አላህ (ዕባዳ) ትርጓሜ መሰረት፣እርሱን እንዲያመልኩና እርሱን ብቻ እንድግገዙት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦





{وَمَا خَلَقۡتُ ٱلۡجِنَّ وَٱلۡإِنسَ إِلَّا لِيَعۡبُدُونِ ﴿٥٦﴾}[الذاريات: ٥٦]

‹‹ጋኔንና ሰውንም፣ሊገዝዙኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም፡፡››[አል ዛሪያት፡56]

ይህን የማያውቅ ሰው ግን በዚህ አለማወቅ እንደተሰቃየ፣ሕይወቱንም በጥርጣሬና በግራ መጋባት ጽልመት እንዳደበዘዘ መኖሩን ይቀጥላል፡፡ ለርሱ ዕባዳና ደስተኝነት የተነጣጠሉ፣ዕባዳ ከዓለማዊ ሕይወቱ ጉዳዮች ጋር፣የዛሬው ዓለም ሕይወትም ከወዲያኛው ሕይወት (ከኣኼራ) ጋር ያልተያያዘ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) በሰማያትና በምድርም ያሉትን ሁሉ ለሰው ልጆች የተገሩ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَسَخَّرَ لَكُم مَّا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِ جَمِيعٗا مِّنۡهُۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّقَوۡمٖ يَتَفَكَّرُونَ ﴿١٣﴾}[الجاثية: ١٣]

‹‹ለናንተም በሰማያት ያለውንና በምድርም ያለውን ሁሉ በመላ ከርሱ ሲኾን የገራላችሁ ነው፤በዚህ ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች ታምራት አለበት፡፡››[አል ጃሢያህ፡13]

የሰው ልጅ በዚህች ምድር ላይ ከምድሪቱና ከራሱ ከሰው እውነተኛ ባለንብረት በኩል፣ለመፈተኛና ለሙከራ ተተኪና ተጠሪው (ኸሊፋ) ተደርጎ ተሹሟል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَهُوَ ٱلَّذِي جَعَلَكُمۡ خَلَٰٓئِفَ ٱلۡأَرۡضِ وَرَفَعَ بَعۡضَكُمۡ فَوۡقَ بَعۡضٖ دَرَجَٰتٖ لِّيَبۡلُوَكُمۡ فِي مَآ ءَاتَىٰكُمۡۗ إِنَّ رَبَّكَ سَرِيعُ ٱلۡعِقَابِ وَإِنَّهُۥ لَغَفُورٞ رَّحِيمُۢ ﴿١٦٥﴾}[الأنعام: ١٦٥]

‹‹እርሱም ያ በምድር ምትኮች ያደረጋችሁ፣በሰጣችሁም ጸጋ ሊፈትናችሁ ከፊሉን በከፊሉ ላይ በደረጃዎች ከፍ ደረገ ነው፤ጌታህ ቅጣቱ ፈጣን ነው፤እርሱም እጅግ መሓሪ ርኅሩህ ነው፡፡››[አል አንዓም፡165]

### 2- ሕይወት፦

የሰው ልጅ የተፈጠረበትን እውነታ ከተረዳ በኋላ፣ከርሱ ጋር ተፈጥሯዊ ቁርኝ ያላት ሕይወት ምንነቷን ለማወቅ ነፍሱ ትቋምጣለች፡፡ ሕይወት የዓለማዊ ደስታዎችና መደሰቻዎች ሁሉ መሰረት እንደ መሆኗ፣ነፍስ የምትፈልጋቸውን ነገሮች ሁሉ



https://www.path-2-happiness.com/am

የማግኘት ተስፋ የተንጠለጠለው በርሷ ላይ ነው። ለመሆኑ የሕይወት ዓለማ ምንድን ነው?! ሕይወትና ሞት የተፈጠሩበት ዓለማ ማንኛው ሰው የተሻለ መልካም ሥራ እንደሚሠራ ለመፈተን ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ٱلَّذِى خَلَقَ ٱلْمَوْتَ وَٱلْحَيَوٰةَ لِيَبْلُوَكُمْ أَيُّكُمْ أَحْسَنُ عَمَلًا ۚ وَهُوَ ٱلْعَزِيزُ ٱلْغَفُورُ ۝٢}[الملك: ٢]

‹‹ያ የትኛችሁ ሥራው ይበልጥ ያማረ መኾኑን ሊሞክራችሁ፣ሞትንና ሕይወትን የፈጠረ ነው፤እርሱም አሸናፊው መሓሪው ነው።››[አል ሙልክ:2]

ይህ እውነታው ነው፤ብዙ ሰዎች ግን አያውቁትም!! አዎ፣ይህ ይህች ዱንያ የተፈጠረችበት ምስጢርና ጥበብ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّمَا مَثَلُ ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَا كَمَآءٍ أَنزَلْنَٰهُ مِنَ ٱلسَّمَآءِ فَٱخْتَلَطَ بِهِۦ نَبَاتُ ٱلْأَرْضِ مِمَّا يَأْكُلُ ٱلنَّاسُ وَٱلْأَنْعَٰمُ حَتَّىٰٓ إِذَآ أَخَذَتِ ٱلْأَرْضُ زُخْرُفَهَا وَٱزَّيَّنَتْ وَظَنَّ أَهْلُهَآ أَنَّهُمْ قَٰدِرُونَ عَلَيْهَآ أَتَىٰهَآ أَمْرُنَا لَيْلًا أَوْ نَهَارًا فَجَعَلْنَٰهَا حَصِيدًا كَأَن لَّمْ تَغْنَ بِٱلْأَمْسِ كَذَٰلِكَ نُفَصِّلُ ٱلْءَايَٰتِ لِقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ ۝٢٤}[يونس: ٢٤]

‹‹የቅርቢቱ ሕይወት ምሳሌ (ጊዜዋ በማጠርና በመጥፋት) ከሰማይ እንዳወረድነው ውሃ፣በርሱም ሰውና እንስሳዎች ከሚበሉት የምድር በቃይ ተቀላቅሎበት (እንደ ፋፋ)፣ምድርም ውበትዋን በያዘችና ባጌጠች ጊዜ፣ባለቤቶቿም በርሷ ላይ እነርሱ ቻዮች መኾናቸውን ባሰቡ ጊዜ፣ትእዛዛችን ሌሊት ወይም ቀን መጥቶባት፣ትላንት እንዳልነበረች የታጨደች፣እንዳደረግናት ብጤ ነው፤እንደዚሁም ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች አንቀጾችን እናብራራለን።››[ዩኑስ:24]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَٱضْرِبْ لَهُم مَّثَلَ ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَا كَمَآءٍ أَنزَلْنَٰهُ مِنَ ٱلسَّمَآءِ فَٱخْتَلَطَ بِهِۦ نَبَاتُ ٱلْأَرْضِ فَأَصْبَحَ هَشِيمًا تَذْرُوهُ ٱلرِّيَٰحُ وَكَانَ ٱللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ مُّقْتَدِرًا ۝٤٥}[الكهف: ٤٥]

የቅርቢቱን ሕይወት ምሳሌ አውሳላቸው፤(እርሷ) ከሰማይ እንዳወረድነው ውሃ፣በርሱም የምድር በቃይ እንደ ተቀላቀለበት፣(ከተዋበ በኋላ ደርቆ)



ነፋሶችም የሚያበኑት ደቃቅ እንደ ኾነ ብጤ ናት፤አላህም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው።››[አል ከህፍ:45]



ዛሬ የምንኖረው ሕይወታችን መተላለፊያ እንጂ ቋሚ የመኖሪያ ስፍራችን አይደለም። ወደ ወዲያኛው የኣኽራ ዘላለማዊ ሕይወት የምታደርሰን መሸጋገሪያ ድልድይ ናት። በመሆኑም ሕይወት በዚህች ዓለም ፍጻሜ አታበቃም፤እውነተኛው የኣኽራ ዘላለማዊ መጭ ሕይወት አለ። የቅርቢቱ ዓለማዊ ሕይወት አላህ (ሱ.ወ.) እንዳለው ሁሉ ጨዋታና ዛዛታ፣ማጌጫና እርስበርስ መፎካከሪያ ብቻ ናት። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ٱعْلَمُوٓا۟ أَنَّمَا ٱلْحَيَوٰةُ ٱلدُّنْيَا لَعِبٌ وَلَهْوٌ وَزِينَةٌ وَتَفَاخُرٌۢ بَيْنَكُمْ وَتَكَاثُرٌ فِى ٱلْأَمْوَٰلِ وَٱلْأَوْلَٰدِ ۖ كَمَثَلِ غَيْثٍ أَعْجَبَ ٱلْكُفَّارَ نَبَاتُهُۥ ثُمَّ يَهِيجُ فَتَرَىٰهُ مُصْفَرًّا ثُمَّ يَكُونُ حُطَٰمًا ۖ وَفِى ٱلْءَاخِرَةِ عَذَابٌ شَدِيدٌ وَمَغْفِرَةٌ مِّنَ ٱللَّهِ وَرِضْوَٰنٌ ۚ وَمَا ٱلْحَيَوٰةُ ٱلدُّنْيَآ إِلَّا مَتَٰعُ ٱلْغُرُورِ ۝٢٠}[الحديد: ٢٠]

‹‹ቅርቢቱ ሕይወት፣ጨዋታና ዛዛታ፣ማጌጫም፣በመካከላችሁም መፎካከሪያ፣በገንዘቦችና በልጆችም ብዛት መበላለጫ ብቻ መኾንዋን ዕወቁ፤(እርሷ) በቃዩ ገበሬዎችን እንደሚያስደስት ዝናም፣ከዚያም በቃዩ እንደሚደርቅና ገርጥቶ እንደሚታየው፣ከዚያም የተሰባበረ እንደሚኾን ብጤ ናት፤በመጨረሻይቱም ዓለም፣ብርቱ ቅጣት፣ከአላህም ምሕረትና ውዴታ አልለ፤የቅርቢቱም ሕይወት መታለያ ጥቅም እንጅ ሌላ አይደለችም።››[አል ሐዲድ:20]

ይህ ቁርኣናዊ አንቀጽ የቅርቢቱን ዓለም ሕይወት በጥቅሉ ደረጃዋን በሚያጣጥል፣በሰው አእምሮ ውስጥ ቦታ በሚያሳጣት አገላለጽ፣የሰው ልጅን ከኣኽራ ሕይወትና ከፋይዳዎቹ ጋር ራሱን እንዲያስተሳስር በሚያደርግ ሁኔታ ያቀርባል። የቅርቢቱ ሕይወት በራሷ ሚዛን ስትለካ ለዓይንና ለእይታ እጅግ የገዘፈ ታላቅ ነገር ሆና ትታያለች። በግዙፉ ዩኒቨርስ ውስጥ ካላት ቦታ አንጻር ስትለካና በኣኽራ ሚዛን ስትመዘን ግን እዚህ ግቢ የማትባል አልባለ ተራ ነገር፣ጨዋታና ዛዛታ፣ማጌጫና በሰዎች መካከል መፎካከሪያ ብቻ ነች። በቁም ነገር የተሞላች፣ትኩረትና ቀልብን በእጅጉ የምትስብ የምር ነገር መስላ ከመታየቷ ጀርባ ያለው እውነታ ግን ይኸው ነው። አዎ . . ይህ የቅርቢቱ ዓለም ሕይወት እውነታ ነው . . እውነታን ለመፈለግ በጥልቀት ሲጓዝ አእምሮ የሚደርስበት እውነታ ነው። ቁርኣን ይህን ሲል ከዓለማዊ ምድራዊ ሕይወት መገለልን፣ምድርን ለሰው ልጆች አገልግሎት መግራትንና ማልማትን፣ወይም የሰው ልጅ የምድር ተጠሪነት ግዴታውን ችላ ብሎ እንዲተው መፈለጉ አይደለም። በዚህ አገላለጹ የሚያነጣጥረው፣የስሜታዊና ስነልቦናዊ እሴቶችን መስፈርቶች በማረም፣በአላፊ




https://www.path-2-happiness.com/am



ጊዜያዊ ደስታዎች ከመሸንገልና ከመንፈሳዊ ምጥቀት አስሮ ከሚያስቀረው መስሕብነታቸው በማስጠንቀቅ ላይ ነው:: ይህች ሕይወት ፍጥረታት ወደ ወዲያኛው የኣኽራ ዘላለማዊ ሕይወት በሚያደርጉት ጉዞ የሚሸጋገሩበት ድልድይ ብቻ ናት:: የዚህች ዓለም ሕይወት አጭር ዕድሜና በፍጥነት ማለፍ ቀጥሎ ከሚመጣው ዘላለማዊነት ጋር ሲነጻጸር ከምንም የሚቆጠር አይደለም:: የወዲያኛው ዓለም ሕይወትም በበኩሉ አንድ ሰው በዚህች የመጀመሪያ ሕይወቱ በሚያሳልፈው ሁኔታ ላይ የተሞረኮዘ ነው:: እናም ዓለማዊ ሕይወቱን የሚያሳልፈው በማያቋርጥ የመፈተኛ ሂደት ውስጥ ነው ማለት ነው:: በዙሪያው የሚመለከታቸው መደሰቻዎች፣አዝናኝና አርኪ ነገሮችም ሆኑ አሳዛኝ፣አሰቃቂና አስጨናቂ ነገሮች ሁሉ ቋሚነት የሌላቸው ቶሎ የሚያበቁ አላፊ ነገሮች እንጂ ሌላ አይደሉም:: ነገ ሁሉም ከነዝርዝር ይዘቶቻቸው ተመዝነው የፈጻሚ እጆችን የመጨረሻ ዕድል ይወስናሉ:: የሥራዎች ዋጋ እንጂ አብሮ ወደ መቃብር የሚወርድ ሌላ ምንም ነገር የለም:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَقَدۡ جِئۡتُمُونَا فُرَٰدَىٰ كَمَا خَلَقۡنَٰكُمۡ أَوَّلَ مَرَّةٖ وَتَرَكۡتُم مَّا خَوَّلۡنَٰكُمۡ وَرَآءَ ظُهُورِكُمۡۖ وَمَا نَرَىٰ مَعَكُمۡ شُفَعَآءَكُمُ ٱلَّذِينَ زَعَمۡتُمۡ أَنَّهُمۡ فِيكُمۡ شُرَكَٰٓؤُاْۚ لَقَد تَّقَطَّعَ بَيۡنَكُمۡ وَضَلَّ عَنكُم مَّا كُنتُمۡ تَزۡعُمُونَ ٩٤}[الأنعام: ٩٤]

‹‹መጀመሪያም ጊዜ እንደ ፈጠርናችሁ ኾናችሁ፣የሰጠናችሁን ሁሉ በጀርባዎቻችሁ ኋላ የተዋችሁ ስትኾኑ፣ለየብቻችሁ ኾናችሁ በእርግጥ መጣችሁን፤እነዚያንም እነሱ በናንተ ውስጥ (ለአላህ) ተጋሪዎች ናቸው የምትሉዋቸውን አማላጆቻችሁን፣ከናንተ ጋር አናይም፤ግንኙነታችሁ፣በእርግጥ ተቋረጠ፤ከናንተም ያ (ያማልደናል) የምትሉት ጠፋ፣(ይባላሉ):፡››[አል አንዓም:94]

አብዛኞቹ ሰዎች ግን ከዚህ እውነታ የተዘናጉ ናቸው:: ይህንኑ በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{يَعۡلَمُونَ ظَٰهِرٗا مِّنَ ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا وَهُمۡ عَنِ ٱلۡأٓخِرَةِ هُمۡ غَٰفِلُونَ ٧}[الروم: ٧]

‹‹ከቅርቢቱ ሕይወት ግልጹን ብቻ ያውቃሉ፤እነርሱም ከኋለኛይቱ ዓለም እነርሱ ዘንጊዎች ናቸው:፡››[አል ሩም:7]

በዚህች አላፊ ሕይወት ረክቶና ወዶ ከፈጣሪ ጌታ ጋር መገናኘትን የማይፈራ ሰው እንዴት ይሆን?! አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّ ٱلَّذِينَ لَا يَرۡجُونَ لِقَآءَنَا وَرَضُواْ بِٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا وَٱطۡمَأَنُّواْ بِهَا وَٱلَّذِينَ هُمۡ عَنۡ ءَايَٰتِنَا غَٰفِلُونَ ٧ أُوْلَٰٓئِكَ مَأۡوَىٰهُمُ ٱلنَّارُ بِمَا كَانُواْ يَكۡسِبُونَ ٨}[يونس: ٧ - ٨]



‹‹እነዚያ መገናኘታችንን የማይፈሩ፣ቅርቢቱንም ሕይወት የወደዱ፣በሷም የረኩ፣እነዚያ እነሱ ከአንቀጾቻችን ዘንጊዎች የኾኑ፣እነዚያ ይሠሩት በነበሩት ምክንያት መኖሪያቸው በእሳት ውስጥ ነው:፡››[ዩኑስ:7-8]

ኣኽራን ትቶ ቅርቢቱንም ሕይወት የመረጠ ሰውስ ምን ይዋጠው?! አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{فَأَمَّا مَن طَغَىٰ ٣٧ وَءَاثَرَ ٱلۡحَيَوٰةَ ٱلدُّنۡيَا ٣٨ فَإِنَّ ٱلۡجَحِيمَ هِيَ ٱلۡمَأۡوَىٰ ٣٩ وَأَمَّا مَنۡ خَافَ مَقَامَ رَبِّهِۦ وَنَهَى ٱلنَّفۡسَ عَنِ ٱلۡهَوَىٰ ٤٠ فَإِنَّ ٱلۡجَنَّةَ هِيَ ٱلۡمَأۡوَىٰ ٤١}[النازعات: ٣٧ـ ٤١]

‹‹የካዳ ሰውማ፣ቅርቢቱንም ሕይወት የመረጠ፣ገሀነም እርሷ በእርግጥ መኖሪያው ናት:: በጌታው ፊት መቆምን የፈራ ሰውማ፣ነፍሱንም ከዝንባሌዋ የከለከለ፣ገነት እርሷ በእርግጥ መኖሪያው ናት:፡››[አል ናዝዓት:37-41]

አዎ፣ሃይማኖታቸውን መሳለቂያና መጫወቻ አድርገው የያዙና በቅርቢቱ ሕይወት የተሸነገሉ ናቸውና አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ٱلَّذِينَ ٱتَّخَذُواْ دِينَهُمۡ لَهۡوٗا وَلَعِبٗا وَغَرَّتۡهُمُ ٱلۡحَيَوٰةُ ٱلدُّنۡيَاۚ فَٱلۡيَوۡمَ نَنسَىٰهُمۡ كَمَا نَسُواْ لِقَآءَ يَوۡمِهِمۡ هَٰذَا وَمَا كَانُواْ بِـَٔايَٰتِنَا يَجۡحَدُونَ ٥١}[الأعراف: ٥١]

‹‹እነዚያ ሃይማኖታቸውን መሳለቂያና መጫወቻ አድርገው የያዙ፣የቅርቢቱም ሕይወት ያታለለቻቸው፣ይህንን ቀናቸውን መገናኘትን እንደረሱ፣በተአምራታችንም ይክዱ እንደ ነበሩ፣ዛሬ እንረሳቸዋለን:፡››[አል አዕራፍ:51]

አዎ፣የአላህ መንገድ መጥመሙንም የሚፈልጉ ናቸውና:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦





https://www.path-2-happiness.com/am



## ጠይቅ . . ቁርኣን መልስ ይሰጠሃል

‹‹ቁርኣንን አጥንቼ በሕይወት ውስጥ ለሚያጋጥሙ ጥያቄዎች ሁሉ መልሶች ያሉት ሆኖ አግኝቸዋለሁ::››

**ማይክል ታይሰን**

**የዓለም የከባድ ሚዛን የቦክክስ ሻምፒዮን**

{ٱلَّذِينَ يَسْتَحِبُّونَ ٱلْحَيَوٰةَ ٱلدُّنْيَا عَلَى ٱلْـَٔاخِرَةِ وَيَصُدُّونَ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِ وَيَبْغُونَهَا عِوَجًا ۚ أُو۟لَٰٓئِكَ فِى ضَلَٰلٍۭ بَعِيدٍ ﴿٣﴾}[إبراهيم: ٣]

‹‹እነዚያ የቅርቢቱን ሕይወት ከመጨረሻይቱ ሕይወት ይበልጥ የሚወዱ፣ከአላህም መንገድ የሚያግዱ፣መጥመሙዋንም የሚፈልጉ ናቸው፤እነዚያ በሩቅ ስሕተት ውስጥ ናቸው::››[ኢብራሂም:3]

ይህ ሁሉ ሲባል ግን የሰው ልጅ ሕይወትን በንቀት ዓይን ይመልከት፣በዕውቀትና በሥራ ምድርን ከማልማት ተቆጥቦ በችጋር እንደ ተቆራመደ ሞቱን ይጠብቅ ማለት አይደለም:: ፈጽሞ እንዲህ ማለት አይደለም:: ተፈላጊው ነገር የዓለማዊ ሕይወት አነዋዋርን አላህ ባስቀመጠው መንገድ ብቻ ማስኬድ ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَٱبْتَغِ فِيمَآ ءَاتَىٰكَ ٱللَّهُ ٱلدَّارَ ٱلْـَٔاخِرَةَ ۖ وَلَا تَنسَ نَصِيبَكَ مِنَ ٱلدُّنْيَا ۖ وَأَحْسِن كَمَآ أَحْسَنَ ٱللَّهُ إِلَيْكَ ۖ وَلَا تَبْغِ ٱلْفَسَادَ فِى ٱلْأَرْضِ ۖ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُحِبُّ ٱلْمُفْسِدِينَ ﴿٧٧﴾}[القصص: ٧٧]

‹‹አላህም በሰጠህ ሀብት የመጨረሻይቱን አገር ፈልግ፤ከቅርቢቱም ዓለም ፋንታህን አትርሳ፤አላህም ወደ አንተ መልካምን እንዳደረገልህ (ለሰዎች) መልካምን አድርግ፤በምድርም ውስጥ ማጥፋትን አትፈልግ፤አላህ አጥፊዎችን አይወድምና፣(አሉት)::››[አል ቀሶስ:77]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَآ أُوتِيتُم مِّن شَىْءٍ فَمَتَٰعُ ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَا وَزِينَتُهَا ۚ وَمَا عِندَ ٱللَّهِ خَيْرٌ وَأَبْقَىٰٓ ۚ أَفَلَا تَعْقِلُونَ ﴿٦٠﴾}[القصص: ٦٠]

‹‹ከማንኛውም ነገር የተሰጣችሁት፤የቅርቢቱ ሕይወት ጥቅምና፣ጌጧ ነው፤አላህ ዘንድ ያለውም (ምንዳ) በጣም በላጭና ዘውታሪ ነው፤አታውቁምን?››[አል ቀሶስ:60]

በዚህ የተሟላ እሳቤ መሰረት የሰው ልጅ ዓለማዊ ሕይወትን ሊጠቀምበት የሚገባው፣እንደ ውድ መገልገያ መሳሪያ ብቻ ይሆናል:: በትክክለኛ መሰረታዊ ምንነቷ ግን ለዘላለማዊው ተድላ የመሸጋገሪያ ድልድይ ከመሆን ያለፍፌ ትኩረት ሊሰጣት አይገባም:: በዚህ ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሙት አላፊ ዓለማዊ ደስታዎች፣ብልልጭ ጊዜያዊ የእርካታ መጠቀሚያዎችና ጌጦች ብቻ ናቸው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{زُيِّنَ لِلنَّاسِ حُبُّ ٱلشَّهَوَٰتِ مِنَ ٱلنِّسَآءِ وَٱلْبَنِينَ وَٱلْقَنَٰطِيرِ ٱلْمُقَنطَرَةِ مِنَ ٱلذَّهَبِ وَٱلْفِضَّةِ وَٱلْخَيْلِ ٱلْمُسَوَّمَةِ وَٱلْأَنْعَٰمِ وَٱلْحَرْثِ ۗ ذَٰلِكَ مَتَٰعُ ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَا ۖ وَٱللَّهُ عِندَهُۥ حُسْنُ ٱلْمَـَٔابِ ﴿١٤﴾}[آل عمران: ١٤]



‹‹ከሴቶችና ከወንዶች ልጆችም፣ከወርቅና ከብር፣ከተከማቹ ገንዘቦችም፣ከተሰማሩ ፈረሶችም፣ከግመል፣ከከብትና ከፍየልም፣ከአዝመራም የኾኑ ፍላጎቶችን መውደድ፣ለሰዎች ተሸለመ፤ይህ ሁሉ የቅርቢቱ ሕይወት መጠቀሚያ ነው፤አላህም እርሱ ዘንድ መልካም መመለሻ (ገነት) አለ::››[ኣሊ ዒምራን:14]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ٱلْمَالُ وَٱلْبَنُونَ زِينَةُ ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَا ۖ وَٱلْبَٰقِيَٰتُ ٱلصَّٰلِحَٰتُ خَيْرٌ عِندَ رَبِّكَ ثَوَابًا وَخَيْرٌ أَمَلًا ﴿٤٦﴾}[الكهف: ٤٦]

‹‹ገንዘብና ወንዶች ልጆች፣የቅርቢቱ ሕይወት ጌጦች ናቸው፤መልካሞቹም ቀሪዎች (ሥራዎች)፣እጌታህ ዘንድ በምንዳ በላጭ ናቸው፤በተስፋም በላጭ ናቸው::››[አል ከህፍ:46]

ዓለማዊ መጠቀሚያዎችም በታዘዘው ተገቢ መንገድ አገልግሎት ላይ እስከ ዋሉ ድረስ በራሳቸው የተጠሉ አይደሉም:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قُلْ مَنْ حَرَّمَ زِينَةَ ٱللَّهِ ٱلَّتِىٓ أَخْرَجَ لِعِبَادِهِۦ وَٱلطَّيِّبَٰتِ مِنَ ٱلرِّزْقِ ۚ قُلْ هِىَ لِلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ فِى ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَا خَالِصَةً يَوْمَ ٱلْقِيَٰمَةِ ۗ كَذَٰلِكَ نُفَصِّلُ ٱلْـَٔايَٰتِ لِقَوْمٍ يَعْلَمُونَ ﴿٣٢﴾}[الأعراف: ٣٢]

‹‹፦ የአላህን ጌጥ፣ያችን ለባሮቹ የፈጠራትን፣ከሲሳይም ጥሩዎቹን፣እርም ያደረገው ማን ነው? በላቸው፤እርሷ በትንሣኤ ቀን ለነዚያ ላመኑት ብቻ ስትኾን፣በቅርቢቱ ሕይወት፣ተገቢያቸው ናት በላቸው፤እንደዚሁ አንቀጾችን እናብራራለን::››[አል አዕራፍ:32]

አንድ ሙስሊም በዚህች ዓለም ላይ ያገኘው ሀብትና ንብረት፣ያጋጠመው ደስታና ሀዘንም ቋሚ አለመሆኑን በእርግጠኝነት ካረጋገጠ በኋላ፣በዚህ እሳቤና በዚህ ግንዛቤ ነው በዓለማዊ ሕይወትና በመደሰቻዎቿ ውስጥ በአስተማማኝ እርምጃ የሚጓዘው:: በመሆኑም ያፈራው ሀብት እጁ ላይ እንጂ ልቡ ውስጥ ገብቶ የተደላደለ አለመሆኑን፣ያመለጠውም ሆነ ያገኘው ዓለማዊ ደስታ የማይጎዳው መሆኑን በተመለከተ ውስጣዊ እምነት ከመቋጠር ጋር፣ ከገደቡ ሳያሳልፍ በልኩ ለመደሰትና ለመጠቀም በማያቋርጥ ጥረት ውስጥ ይኖራል ማለት ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{مَآ أَصَابَ مِن مُّصِيبَةٍ فِى ٱلْأَرْضِ وَلَا فِىٓ أَنفُسِكُمْ إِلَّا فِى كِتَٰبٍ مِّن قَبْلِ أَن نَّبْرَأَهَآ ۚ إِنَّ ذَٰلِكَ عَلَى ٱللَّهِ يَسِيرٌ ﴿٢٢﴾ لِّكَيْلَا تَأْسَوْا۟ عَلَىٰ مَا فَاتَكُمْ وَلَا تَفْرَحُوا۟ بِمَآ ءَاتَىٰكُمْ ۗ وَٱللَّهُ لَا يُحِبُّ كُلَّ مُخْتَالٍ فَخُورٍ ﴿٢٣﴾}[الحديد: ٢٢- ٢٣]

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

‹‹በምድርም፣በነፍሶቻችሁም፣መከራ (ማንንም) አትነካም፣ሳንፈጥራት በፊት በመጽሐፍ የተመዘገበች ብትኾን እንጅ፤ይህ በአላህ ላይ ገር ነው። (ይህ ማሳወቃችን) ባመለጣችሁ ጸጋ ላይ እንዳታዝኑ፣አላህም በሰጣችሁ ነገር (በትዕቢት) እንዳትደሰቱ ነው፤አላህም ኩራተኛን፣ጉረኛን ሁሉ አይወድም።››[አል ሐዲድ፡22-23]

በዚህም በመደሰቻዎች፣በመጠቀሚዎችና በፍላጎት ማርኪዎች ይጠቀምና ከአላህ (ሱ.ወ.) ምንዳ ያገኝበታል። ዓለማዊ ሕይወትና የወዲያኛው የኣኺራ ሕይወት፣አካላዊና ሥጋዊ ደስታ ከመንፈሳዊና ሕሊናዊ ደስታ ጋር፣ደስተኝነትና መታደል ከዓለማዊ መደሰቻዎች ጋር፣ደስተኛነትና ውስጣዊ እፎይታም እርሱ ዘንድ እርስ በርስ የተሳሰሩ ይሆናሉ።

## 3- ዩኒቨርስ

ሙስሊም ሰው በዩኒቨርስ ግንዛቤ አስተውሎው ወደ ሦስተኛውና የመጨረሻው ምዕራፍ የሚሸጋገር ሲሆን፣ይህም በዚሪያው ያለው መላው ፍጥረተ ዓለምና ሕላዌ ነው። የሚቀጥለውን የአላህ (ሱ.ወ.) ቃል በማስተዋልና በመስተንንም ይጀምረል፦

{قُلِ ٱنظُرُواْ مَاذَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۚ وَمَا تُغۡنِي ٱلۡأٓيَٰتُ وَٱلنُّذُرُ عَن قَوۡمٖ لَّا يُؤۡمِنُونَ ١٠١} [يونس: ١٠١]

‹‹፦ በሰማያትና በምድር ያለውን (ታምር) ተመልከቱ፣በላቸው፤ታምራቶችና አስፈራሪዎችም፣ለማያምኑ ሕዝቦች አይጠቅሙም።››[ዩኑስ፡ 101]

በማስከተልም ቀደም ሲል ባደረገው አስተውሎና ማስተንተን፣የተፈጠረበትን ዓለማና የመኖሩን እውነታ አስመልክቶ ከደረሰበት ውጤት ጋር ተመሳሳይ ወደ ሆነ ውጤት ይደርስ ዘንድ የአላህን (ሱ.ወ.) ፍጥረታትና ድንቅ ሥራዎቹን እንዲያስተውልና እንዲያስተነትን ጥሪ የሚያደርጉ በአስርቶች የሚቆጠሩ ቁርኣናዊ አንቀጾችን ማጥናት ይቀጥላል። ስለ ዩኒቨርስ የሚኖረው ግንዛቤም ሁለት የተሟሉ እውነታዎችን ከመረዳት መንደርደር



እንዳለበትም ግልጽ ይሆንለታል። እነሱም፦

አንደኛው እውነታ፦ አላህ (ሱ.ወ.) በአካባቢው የሚገኙ አብዛኞቹን ነገሮች ለርሱ ግልጋሎት የገራለት የመሆኑ እውነታ ነው። ስለሆነም ለርሱ የተሰጠው ብልጫ በአንዳንድ ልዩ መለዮዎቹ ብቻ ላይ የተወሰነ ሳይሆን፣እነዚህን ፍጥረታት ለርሱ ጥቅም፣ብልጽግናውንና እድገቱን እውን ለማድረግ ለግልጋሎቱ የተገሩለት ወደማድረግም የሚሸጋገር ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{أَلَمۡ تَرَوۡاْ أَنَّ ٱللَّهَ سَخَّرَ لَكُم مَّا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِ وَأَسۡبَغَ عَلَيۡكُمۡ نِعَمَهُۥ ظَٰهِرَةٗ وَبَاطِنَةٗۗ وَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن يُجَٰدِلُ فِي ٱللَّهِ بِغَيۡرِ عِلۡمٖ وَلَا هُدٗى وَلَا كِتَٰبٖ مُّنِيرٖ ٢٠}[لقمان: ٢٠]

‹‹አላህ በሰማያት ያለውንና በምድርም ያለውን ሁሉ፣ለናንተ ያገራላችሁ፣ጸጋዎቹንም ግልጽም ድብቅም ሲኾኑ የሞላላችሁ፣መኾኑን አታዩምን? ከሰዎችም ያለ ዕውቀትና ያለ መሪ፣ያለ ግልጽ መጽሐፍም በአላህ የሚከራከር አልለ።››[ሉቅማን፡20]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلَّيۡلَ وَٱلنَّهَارَ وَٱلشَّمۡسَ وَٱلۡقَمَرَۖ وَٱلنُّجُومُ مُسَخَّرَٰتُۢ بِأَمۡرِهِۦٓۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّقَوۡمٖ يَعۡقِلُونَ ١٢}[النحل: ١٢]

‹‹ለናንተም ሌሊትንና ቀንን፣ፀሐይና ጨረቃንም፣ገራላችሁ፤ከዋክብትም በፈቃዱ የተገሩ ናቸው፤በዚህ ውስጥ ለሚያውቁ ሕዝቦች በእርግጥ ታምራቶች አልሉ።››[አል ነሕል፡12]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{هُوَ ٱلَّذِي جَعَلَ لَكُمُ ٱلۡأَرۡضَ ذَلُولٗا فَٱمۡشُواْ فِي مَنَاكِبِهَا وَكُلُواْ مِن رِّزۡقِهِۦۖ وَإِلَيۡهِ ٱلنُّشُورُ ١٥}[الملك: ١٥]


‹‹እርሱ ያ ምድርን ለናንተ የተገራች ያደረገላችሁ ነው፤በጋራዎችና በመንገዶችዋም ኺዱ፣ከሲሳዩም ብሉ፤(ኋላ) መመለሻውም ወደርሱ ብቻ ነው።››[አል ሙልክ፡ 15]

ሙስሊሙ በብዙ ቁርኣናዊ አንቀጾች ውስጥ ይህ ዩኒቨርስና ያጠቃለላቸው ነገሮች ሁሉ ለርሱ ጥቅም የተገሩ መሆናቸውን የሚያመለክቱ አንጸባራቂ ማስረጃዎችን ያገኛል። ይህም ዩኒቨርስን መላመድና ለጥቅሙ መግራት ለሰው ልጅ የግድ አስፈላጊ መሆኑን የሚጠቁም ሲሆን፣በውስጡ ሊደርሱ በሚችሉ አደጋዎችና አስቸጋሪ

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am





## የሰብአዊነት ሃይማኖት

‹‹ሙሉ ሕይወቴ ያጣሁትን ራሴን እስላም ውስጥ አገኘሁ፤በዚያ ቅጽበትም ለመጀመሪያ ጊዜም ሰው መሆኔ ተሰማኝ። ከሰው ልጅ ተፈጥሮ ጋር የተጣጣመ በመሆኑ ሰውን ወደ ‹‹ሰውነት›› ተፈጥሮው የሚመልስ ሃይማኖት ነው።፡››

**ማርቲን ሌንግዝ**

**እንግሊዛዊ ፈላስፋ**

ሁኔታዎች ተስፋ መቁረጥ የተከለከለ መሆኑንም በውስጡ ይዟል። እናም ተፈጥሮ ለደካማው የሰው ልጅ የማያቋርጥ ፈታኝ ባለጋራ አይደለችም፤ሰውም በፊናው ተፈጥሮን ለጥቅሙ በመግራት ላይ እንጂ ሙሉ ለሙሉ በቁጥጥሩ ስር ለማዋል የማያቋርጥ ትግል በማድረግ ላይ አይደለም።

ሁለተኛው እውነታ፦ ዩኒቨርስ ምስጢራቱን ሙሉ በሙሉ ለሰው ልጅ ገና ያልገለጠ የመሆኑ እውነታ ነው። የተገሩለትና ያሳካቸው ብዙ ነገሮች ቢኖሩም የዩኒቨርሱ ሌሎች አያሌ ጎኖች ከሰው ልጆች ግንዛቤ ከዕውቀቱና ከቁጥጥሩ ውጭ ናቸው። ፍጥረተ ዓለም በመላእክትና በጋኔኖች (በጅንን) የተሞላ ነው። የሰው ልጅ ትክክለኛ ምንነታቸውን ብቻ ሳይሆን መኖራቸውንም ጭምር ለማወቅ ከግንዛቤው ውጭ የሆኑ ሌሎች ፍጥረታትም ሊኖሩ ይችላሉ። ከዚህ ዩኒቨርስ ታላቅ ግዝፈት አንጻር የሰው ልጅ በውስጡ የሚይዘው ቦታ ይህ ነው ሊባል ከማይችል አንዲት የአቶም ቅንጣት የሚያክል አይደለም።


በነዚህ ሁለት እውነታዎችም ሙስሊሙ በዙሪያው ስላለው ዩኒቨርስ ያለው እይታ የተሟላ ይሆናል። ከተቀሩት ፍጥረታት መካከል የተሰጠውን ልዩ ቦታም በሚገባ ይገነዘባል። አላህ (ሱ.ወ.) ሰውን፣በውስጡ የሚገኙ አብዛኞቹ ፍጥረታትን ለርሱ የተገሩ ያደረገው ዩኒቨርስና የመላው ፍጥረተ ዓለም ማዕከል አድርጎታል። በተመሳሳይ መልኩም በዩኒቨርሱ ውስጥ አንዳንዶቹ በሮች ለርሱ ዝግ የመደረጋቸውን፣እጹብ ድንቅ ተሰጥኦውና ድንቅ ችሎታው የፈለገውን ያህል ቢመጥቅ እነዚያን በሮች ማንኳኳት ፈጽሞ የማይችል የመሆኑን እውነታም ይገነዘባል።

የሰው ልጅ በዙሪያው ከሚገኙት ጋር የሚኖረውን ግንኙነት በላቀ የጨዋነት ባሕርይና ምሉእ በሆኑ ስነምግባሮች የሚመራ መሆን አለበት። ግንኙነቶቻቸውን በሥርዓተ አልበኝነት የሚመሩ ግለሰቦች፣ለደንብና ለመመሪያ የማይገዛ ሚዘናዊ ያልሆነ ግንኙነት ስለሚኖራቸው ሁሌም የችግር፣የስቃይና ያልተገራ ሻካራ ሕይወት ይመራሉ። ከሌሎች ጋር ያላቸው ትስስር በራስ ወዳድነት፣በምቀኝነት፣በክፉ ጥርጣሬ፣በሴረኝነትና በመጠላለፍ . . ላይ የተመሰረተ ነው። ይህ ሁሉ የሰውን ልጅ ደስተኝነትና እፎይታን የሚነሳው ሲሆን፣ሁሌም በማያቋርጥ የጭንቀት፣የድብርት፣የውጥረት ሁኔታ ውስጥ እየተሰቃየ እንዲኖር ያደርገዋል። እናም እፎይታና ደስተኝነት ከወዴት አባቱ?! አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَا تَسْتَوِى ٱلْحَسَنَةُ وَلَا ٱلسَّيِّئَةُ ۚ ٱدْفَعْ بِٱلَّتِى هِىَ أَحْسَنُ فَإِذَا ٱلَّذِى بَيْنَكَ وَبَيْنَهُۥ عَدَٰوَةٌ كَأَنَّهُۥ وَلِىٌّ حَمِيمٌ ﴿٣٤﴾ وَمَا يُلَقَّىٰهَآ إِلَّا ٱلَّذِينَ صَبَرُوا۟ وَمَا يُلَقَّىٰهَآ إِلَّا ذُو حَظٍّ عَظِيمٍ ﴿٣٥﴾} [فصلت: ٣٤-٣٥]

**‹‹መልካሚቱና ክፉይቱም (ጠባይ) አይተካከሉም፤በዚያች እርሷ መልካም በኾነችው ጠባይ (መጥፎይቱን) ገፍትር፤ያን ጊዜ ያ ባንተና በርሱ መካከል ጠብ ያለው ሰው፣እርሱ ልክ እንደ አዛኝ ዘመድ ይኾናል።፡››**[ሓ.ሚም አልሰጅዳህ፡34-35]

ሕይወቱንና ግንኙነቶቹን በመብትና ግዴታ መርሕ ላይ ያደራጀው ሰው ግን ግዴታዎቹን እየፈጸመና፣መብቶቹን በገዛ ፈቃዱ ለቀቅ እያደረገ፣ያጠፉበትንም በይቅርታ እያለፈ ኑሮውን ይመራል።



## የሰብአዊ ክብርና የስነምግባር ሃይማኖት

‹‹ለዚህ ነው እስላምን የመረጥኩት፤በአጸዱና በጥላው ስር ደስተኝነትና እርካታ ይሰማኝ ዘንድ . . መንፈስን ከገላ የማይነጥል፣ነፍስንም ከሥጋ የማይለይ ሃይማኖት መከተሌ ይታወቀኝ ዘንድ በእርግጥ እስላምን ተቀብያለሁ። እስላም መልካም ስነምግባርንና በርሱ መታነጽን የሚያበረታታና ወደዚያ የሚገፋፋ፣ለሰብአዊ ክብርና ለጥበቃው ጥሪ የሚያደርግ የጠራ ሃይማኖት መሆኑ ለኔ በቂዬ ነው። ለዚህም ስል ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩንና ሙሐመድም ባሪያውና መልክተኛው መሆናቸውን መስክሬያለሁ፣በዚህ ላይ ሆኜም ከጌታዬ ጋር እገናኛለሁ።፡››

**ፋታን ሞሴይህ**

**ፈረንሳዊ ፈላስፋ**



ይህን በማድረጉም ያለጥርጥር ደስተኛ ሰው ይሆናል። ውዴታ ከመሰል ሰብአዊ ፍጡራን ጋር በሚኖረው በይነሰባዊ ግንኙነት ውስጥ በሚኖሩት ደረጃዎች ቁንጮ ደረጃ ይይዛል። ውዴታ፡- ፍቅር፣መግባባት፣አብሮነትና መተሳሰብ ማለት ነውና። የሰው ልጅ የተስተካከለ ሚዛናዊ ተፈጥሮም ይህ ነው።

## የደስተኝነት መንገድ . . የሰው ልጅ ከራሱ፣ከሕይወትና ከፍጥረተ ዓለሙም ጋር የሚያደርገው እርቅ ነው፦

የሰው ልጅ በዚህ እምነቱ ከፈጣሪው፣ከገዛ ራሱና በዙሪያው ካለው ፍጥረተ ዓለም ጋር ይታረቃል። በቅድሚያ ለአላህ (ሱ.ወ.) አገልጋይ ባሪያ የመሆኑን እውነታ የሚገነዘብና ተገቢ ግዴታዎቹን በመፈጸም ላይ የተሰማራ ነው። ሁለተኛም የተቀሩ ፍጥረታትን ለርሱ ጥቅም የተገሩ በማድረግ አላህ (ሱ.ወ.) ያከበረው ፍጡር የመሆኑን እውነታ በማወቁ የራሱን ልክና ደረጃ የሚረዳ፣ለርሱ ወደ ተፈጠረው ጀነት ከመመለሱ በፊት ይፈተን ዘንድ ወደ መሬት የወረደ መሆኑን፣ይህችን ምድር የማልማትና ለሰው ልጆች ኑሮ ገር የማድረግ ኃላፊነት የተሰጠው መሆኑንም የሚገነዘብ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{هُوَ أَنشَأَكُم مِّنَ ٱلۡأَرۡضِ وَٱسۡتَعۡمَرَكُمۡ فِيهَا فَٱسۡتَغۡفِرُوهُ ثُمَّ تُوبُوٓاْ إِلَيۡهِۚ إِنَّ رَبِّي قَرِيبٞ مُّجِيبٞ ٦١}

[هود: ٦١]

‹‹እርሱ ከምድር ፈጠራችሁ፤ በውስጧ እንድታለሙዋትም አደረጋችሁ፤ ምሕረቱንም ለምኑት፤ከዚህም ወደርሱ ተመለሱ፤ጌታዬ ቅርብ፣(ለለመነው) ተቀባይ ነውና አላቸው።››[ሁድ፡61]

በተጨማሪም ሥጋዊ ፍላጎቶቹን ሸሪዓው ባስቀመጠው ገደብና አስፈላጊ በሆነ መጠን ብቻ መጠቀምን ራሱን እንዲያለማምድና እንዲያሰለጥንም ኃላፊነት ተጥሎበታል። ፈጣሪ አምላክን፣ነፍስንና ፍጥረተ ዓለምን በተመለከተ ወደዚህ የተሟላ ግንዛቤ ከደረስን ዘንዳ፣ይህንን ግንዛቤ በተግባር በመተርጎም ልንደርስበት የምንችለው ውጤት ምን እንደሚሆን መጠየቅ አሁን ተገቢያችን ይሆናል። የሰው ልጅ ይህንን እውነታ ከተገነዘበ በኋላ ደስተኝነት በሁለቱም ሕይወቶች ማለትም በዱንያና በኣኺራም፣ከአላህ (ሱ.ወ.) ውዴታ፣ትእዛዛቱን ከመፈጸምና እርሱ ባስቀመጠው ገደብ ውስጥ ከመወሰን . . ጋር የተቆራኘ ነው። የአካልና የነፍስ ፍላጎቶችን፣የግለሰብና የማሕበረሰብ ፍላጎቶችንም፣የዱንያ ሕይወት ግንባታንና የኣኺራ ሕይወት ግንባታንም ሚዛናዊና ተመጣጣኝ በማድረግ ብቻ ይደረስበታል። ዱንያ የትግል፣የሥራና የመፈተኛ አገር በመሆኗ በዚህች ዓለም ላይ ሊገኝ የሚችለው ተድላና ደስተኝነት ደረጃው ያሻውን ያህል ቢሆን ጎደሎ



### የእስላም ጸጋ

‹‹አንድ ሰው ከሚረካባቸው ጸጋዎች መካከል፣አላህ ልቡን ለእስላም ክፍት አድርጎ ከሚያሰፋለት ጸጋ የሚበልጥበት በዚህ ዓለም ላይ የለም። በብርሃኑ ተመርቶ የዛሬውን ዓለም ሕይወትና የወዲያኛውን ዓለም ሕይወት እውነታዎች ለመመልከት ይበቃል። በዚህም እውነትን ከሐሰት፣የመታደልንም መንገድ ከዕድለ ቢስነት መንገድ ይለያል። አላህ ለቸረኝ፣ውስጤን በደስተኝነት በሞላው፣በዚህ የተንዠረገገና በፍሬ ዓይነቶች በተሞላ ታላቅ ጥላ - በእስላም ውስጥ ያለው የእስላማዊ ቤተሰብነትና ወንድማማችነት ጥላ ስር የማረፍ ዕድል ላጎናጸፈኝ አምላክ፣እርሱን ለማመስገን በፊቴ እደፋለሁ።››

**ማርሼላ ማይክል አንጅሎ**
**እንግሊዛዊት ተዋናይት**






https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

መሆኑን፣የወዲያኛው የኣኼራ ሕይወት የምርመራ አገር በመሆኑ ምርመራውን በስኬት ያለፈ ሰው ዘላለማዊውንና ምሉእ የሆነውን ተድላና ደስተኘነት የሚጎናጸፍ መሆኑን ወደሚያረጋግጥ ድምዳሜ መድረሱ የግድ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{يُبَشِّرُهُمْ رَبُّهُم بِرَحْمَةٍ مِّنْهُ وَرِضْوَانٍ وَجَنَّاتٍ لَّهُمْ فِيهَا نَعِيمٌ مُّقِيمٌ ﴿٢١﴾ خَالِدِينَ فِيهَا أَبَدًا إِنَّ اللَّهَ عِندَهُ أَجْرٌ عَظِيمٌ ﴿٢٢﴾}[التوبة: ٢١-٢٢]

‹‹ጌታቸው ከርሱ በኾነው እዝነትና ውዴታ በገነቶችም ለነሱ በውስጥዋ የማያቋርጥ መጠቀሚያ ያለባት ስትኾን ያበስራቸዋል።››[አል ተውበህ:21-22]

የሰው ልጅ እርጋታና እርካታ ይሰማው ዘንድ፣በዱንያና በኣኼራም ጥሩ ሕይወት ለመኖር፣ኢማንና መልካም ሥራ የግድ አስፈላጊ ይሆናሉ። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{مَنْ عَمِلَ صَالِحًا مِّن ذَكَرٍ أَوْ أُنثَىٰ وَهُوَ مُؤْمِنٌ فَلَنُحْيِيَنَّهُ حَيَاةً طَيِّبَةً وَلَنَجْزِيَنَّهُمْ أَجْرَهُم بِأَحْسَنِ مَا كَانُوا يَعْمَلُونَ ﴿٩٧﴾}[النحل: ٩٧]

‹‹ከወንድ ወይም ከሴት፣እርሱ አማኝ ኾኖ በጎን የሠራ፣መልካም ኑሮን በእርግጥ እናኖረዋለን፤ይሠሩትም ከነበሩት ነገር በመልካሙ ምንዳቸውን እንመነዳቸዋለን።››[አል ነሕል:97]



## የደስተኘነት መንገድ ጠቋሚ ምልክት፦

በአላህ (ሱ.ወ.) የማመን መንገድ የሆነውን እውነተኛውን የደስተኘነት መንገድ እስኪ እንተዋወቅ። በጉዞው ወቅት የተረጋጋንና ኃያል ወኔ የሰነቅን እንሆን ዘንድ፣የዚህ መንገድ አቅጣጫ አመላካች የሆኑ አንዳንድ ጠቋሚ ምልክቶችን ማብራራት ተገቢ ይሆናል፦

### 1- የአላህ (ሱ.ወ.) መንገድ ነው፦

አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦


{وَأَنَّ هَٰذَا صِرَاطِي مُسْتَقِيمًا فَاتَّبِعُوهُ وَلَا تَتَّبِعُوا السُّبُلَ فَتَفَرَّقَ بِكُمْ عَن سَبِيلِهِ ذَٰلِكُمْ وَصَّاكُم بِهِ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ ﴿١٥٣﴾}[الأنعام: ١٥٣]

‹‹ይህም ቀጥተኛ ሲኾን መንገዴ ነው፤ተከተሉትም፤(የጥመት)መንገዶችንም አትከተሉ፤ከ(ቀጥተኛው) መንገዱ እናንተን ይለያዩዋችኋልና። ይኻችሁ ትጠነቀቁ ዘንድ በርሱ አዘዛችሁ።››[አል አንዓም:153]

እናም የደስተኘነትና የመታደል መንገድ የአላህ (ሱ.ወ.) መንገድ፣ለፍጡራን አገልጋዮቹ ያስተላለፋቸው - እርሱ የሚበጃቸውን ከሁሉም በላይ ዐዋቂ ነና - መመሪያዎቹ ነው። የአላህን መንገድ የሚተውና በተለያዩ ሰው ሠራሽ መንገዶች ደስተኘነትንና መታደልን የሚመኝ ሰው፣ያልታደለ መናጢ መሆኑ ጥርጥር የለውም። ከርሱ መንገድ ውጭ በምንም ዓይነት ተድላና ደስተኘነት ሊሞኖር አይችልም። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{فَمَنِ اتَّبَعَ هُدَايَ فَلَا يَضِلُّ وَلَا يَشْقَىٰ ﴿١٢٣﴾ وَمَنْ أَعْرَضَ عَن ذِكْرِي فَإِنَّ لَهُ مَعِيشَةً ضَنكًا وَنَحْشُرُهُ يَوْمَ الْقِيَامَةِ أَعْمَىٰ ﴿١٢٤﴾}[طه: ١٢٣-١٢٤]

‹‹ከኔም የኾነ መሪ ቢመጣላችሁ፣መሪየን



**እምነትና የስነልቦና ጤንነት**

‹‹ባለፉት ሠላሳ ዓመታት ውስጥ የከሰለጠነው ዓለም ሕዝቦች የተለያዩ ግለሰቦች የምክር አገልግሎት ሰጥቻለሁ።በመቶዎች የሚቆጠሩ ሕሙማንን አክሜያለሁ። በመካከለኛው የዕድሜ ክልል ማለትም ሰላሳ አምስት ዓመት ከሆናቸው መካከል የችግሩ መንሥኤና የሕመሙ መነሻ ኢአማኝነትና በሃይማኖት ትምህርቶች ላይ ማመጽ ያልሆነ አንድም አልገጠመኝም። እያንዳንዱ ታማሚ የበሽታው ሰለባ የሆነው ሃይማኖት የሚያስገኘውን የመንፈስ እርካታና ውስጣዊ መረጋጋት የተነፈገ በመሆኑ ነው ማለት ይቻላል። ከነዚህ መካከል ወደ እምነቱ ተመልሶ ሕይወትን ለመጋፈጥ በሃይማኖት ትእዛዛትና እገዳዎች ሳይታገዝ የተፈወሰ አንድም ሰው አልነበረም።

ካርል ቢዮንግ

ታዋቂ ሳይካትሪስት

የተከተለ አይሳሳትም፤አይቸገርምም። ከግሣጼየም የዞረ ሰው፣ለርሱ ጠባብ ኑሮ አልለው፤በትንሣኤም ቀን ዕውር ኾኖ እንቀሰቅሰዋለን።››[አል ጣሃ፡123-124]

ደስተኝነትና መታደል የርሱን መንገድ ለያዘና መመሪያውን ለተከተለ ሰው ብቻ ነው። ዘላለማዊ ዕድለ ቢስነትና ስቃይ ደግሞ ከስመ ገናና ታዋቂ ከዋክብት አንዱ ተደርጎ ቢታይ እንኳ፣ከመንገዱ ፊቱን ያዞረና ከርሱ ያፈነገጠ ሰው ዕጣ ፈንታ ነው።

## 2- አካላዊ ደስታንና መንፈሳዊ ደስታን የሚያጠቃልል መንገድ ነው፦

ሰው የሥጋና የነፍስ ውሑድ መሆኑ ይታወቃል። ሁለቱም የየራሳቸው የሆነ ቀለብ አላቸው። አንዳንድ መንገዶችና ፍልስፍናዎች ለነፍስ ፍላጎቶች ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ሥጋዊ ፍላጎቶችን በከፍተኛ ደረጃ ያጣጥላሉ። ይህም ታላቅ አደጋን አስከትሏል። ዘመናዊው ቁስ አካላዊነት ደግሞ በተቃራኒው የመንፈስና የነፍስ ፍላጎቶችን ከነአካቴው ውድቅ አድርጎ ለሥጋ ወይ ለገላ ብቻ የሚፈልገውን ሁሉ ሰጠ። በዚህም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ሰብአዊ ፍጡራን ለሥጋዊ ፍላጎቶችና ለአካላዊ መደሰቻዎች ብቻ ወደ ተፈጠሩ እንስሳት ደረጃ እንዲዘቅጡ ተደረገ! ወይም ወደ ግኡዝ ቁሳቁስነት ተቀየሩ። የእስላም መንገድ ግን ነፍስና መንፈስን በመለኮታዊ ብርሃን ይቀልባል፤አካልንም ይንከባከባል፤ፍላጎቶቹን ጥሩና ሐላል በሆነ ማርኪያ ያጠግባል፦

{وَٱبۡتَغِ فِيمَآ ءَاتَىٰكَ ٱللَّهُ ٱلدَّارَ ٱلۡأٓخِرَةَۖ وَلَا تَنسَ نَصِيبَكَ مِنَ ٱلدُّنۡيَاۖ وَأَحۡسِن كَمَآ أَحۡسَنَ ٱللَّهُ إِلَيۡكَ} [القصص: ٧٧]

‹‹አላህም በሰጠህ ሀብት የመጨረሻይቱን አገር ፈልግ፤ከቅርቢቱም ዓለም ፋንታህን አትርሳ፤አላህም ወደ አንተ መልካምን እንዳደረገልህ (ለሰዎች) መልካምን አድርግ፤››[አል ቀሶስ፡77]

ነቢዩ ﷺ፣ሰልማን አልፋሪሲ (ረ.ዐ.)፦ ‹‹ለፈጣሪ ጌታህ ግዴታ አለብህ፤ለራስህ ነፍስም ግዴታ አለብህ፣ለቤተሰብህም ግዴታ አለብህ፣እናም ለሁሉም ባለመብት ተገቢውን ፈጽም።›› [በቡኻሪ የተዘገበ] ያሉትን አባባል ተቀብለው አጽድቀዋል።

## 3- የደስተኝነትና የጀግንነት መንገድ ነው፦

የኢማንን ጥፍጥና የቀመሰ ሰው፣አንገቱ ላይ ጎራዴ ቢደረግ እንኳ ፈጽሞ ሊተወው አይችልም። የፈርዖን ድግምተኞች አምነው የመታደለን መንገድ ሲይዙ ፈርዖን እንዴት እንደዛተባቸው ተመልከቱ፤ቁርኣን ውስጥ እንደሚከተለው ቀርቧል፦

{فَلَأُقَطِّعَنَّ أَيۡدِيَكُمۡ وَأَرۡجُلَكُم مِّنۡ خِلَٰفٖ وَلَأُصَلِّبَنَّكُمۡ فِي جُذُوعِ ٱلنَّخۡلِ وَلَتَعۡلَمُنَّ أَيُّنَآ أَشَدُّ عَذَابٗا وَأَبۡقَىٰ ٧١}[طه: ٧١]

‹‹እጆቻችሁንና እግሮቻችሁን በማናጋት (ግራና ቀኝን በማፈራረቅ) እቆርጣችኋለሁ፤በዘምባባም ግንዶች ላይ እሰቅላችኋለሁ፤ማንኛችንም ቅጣቱ በጣም ብርቱ፣የሚቆይም መኾኑን ታውቃላችሁ አላቸው።››[ጣሃ፡71]

ምላሻቸው ግን በጽናት የተሞላ ነበር፦

{قَالُواْ لَن نُّؤۡثِرَكَ عَلَىٰ مَا جَآءَنَا مِنَ ٱلۡبَيِّنَٰتِ وَٱلَّذِي فَطَرَنَاۖ فَٱقۡضِ مَآ أَنتَ قَاضٍۖ إِنَّمَا تَقۡضِي هَٰذِهِ ٱلۡحَيَوٰةَ ٱلدُّنۡيَآ ٧٢} [طه: ٧٢]

‹‹ከመጡልን ታምራቶችና ከዚያም ከፈጠረን (አምላክ)፣ፈጽሞ አንመርጥህም፤አንተም የምትፈርደውን ፍረድ፤የምትፈርደው በዚች በአነስተኛይቱ ሕይወት ብቻ ነው አሉ።››[ጣሃ፡72]

የደስተኝነትን መንገድ መርጠው ከያዙ ከአጭር ጊዜ በኋላ ይህን የመሰለ ጽናት የተላበሱት፣የዚህን ኢማን ጥፍጥና ስለቀመሱና በአመለካከታቸውና በውሳኔያቸውም ግልጽ የሞት ዛቻና አደጋ በታጋረጠባቸው ሁኔታ ውስጥ እንኳ ይበልጥ ጽኑና እርግጠኞች እንዲሆኑ ስለ አደረጋቸው ነው።

## 4- ደስተኝነት ውስጣዊ መረጋጋትና የልብ እፎይታ ነው፦

ያለ ሕሊና ዕረፍት፣ያለ ውስጣዊ መረጋጋትና እፎታ ደስተኝነት አይኖርም። እነዚህ ደግሞ ኢማን በሌለበት የሚታሰቡ አይደሉም። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{هُوَ ٱلَّذِيٓ أَنزَلَ ٱلسَّكِينَةَ فِي قُلُوبِ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ لِيَزۡدَادُوٓاْ إِيمَٰنٗا مَّعَ إِيمَٰنِهِمۡۗ وَلِلَّهِ جُنُودُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۚ وَكَانَ ٱللَّهُ عَلِيمًا حَكِيمٗا ٤}[الفتح: ٤]

‹‹እርሱ በምእመናን ልቦች ውስጥ ከእምነታቸው ጋር እምነትን ይጨምሩ ዘንድ፣እርዳታን ያወረደ ነው፤ለአላህም የሰማያትና የምድር ሰራዊቶች አልሉት፤አላህም ዐዋቂ ጥበበኛ ነው።››[አል ፈትሕ፡4]

እምነት በሁለት በኩል ደስተኝነትን ያስገኛል። አንደኛ፦ የዕድለ ቢስነትና የመናጢነት አደገኛ መንስኤዎች በሆኑት በኃጢኣትና በወንጀል አረንቋ ውስጥ ከመዘፈቅ ይጠብቃል። አንድ ሰው ልቡ በፈጣሪ አምላኩ ከማመን የተራቆተ እስከሆነ ድረስ፣አንድን ሰው ሥጋዊ ፍላጎቶቹና እኩይ ዝንባሌዎቹ ወደ




### አጥጋቢ ምላሽ

‹‹ለመንፈስና ቁስ አካል አስቸጋሪ ጥያቄዎች እስላም ውስጥ አርኪና አሳማኝ መልሶችን አግኝቻለሁ። ልክ እንደ ነፍስና እንደ መንፈስ ሁሉ ለአካልም መፈጸም ያለብን ግዴታ እንዳለብንም ለማወቅ በቅቻለሁ። በእስላም አመለካከት አካላዊ ፍላጎቶች፣የሰው ልጅ ጠንካራ፣አምራችና ንቁ ሆኖ ይኖር ዘንድ ሊረኩ የሚገቡ ተፈጥሯዊ ፍላጎቶች ናቸው። እስላም ለነፍስ እርካታን እውን በሚያደርግና በአላህ ትእዛዛት እንድትገዛ በሚያስችላት ጤናማ መደላድል ላይ የታነጹ መሰረታዊ መርሆዎችን አኑሯል። ለአብነት ያህል ጋብቻ እስላም ውስጥ ወሲባዊ ፍላጎቶችን ለማርካት ብቸኛው መንገድ ነው። ሶላት፣ጾም፣አምልኮዎችና በአላህ ማመን ደግሞ የሰውን ልጅ መንፈሳዊ ጎን የሚያረኩ መሳሪያዎች ናቸው። በዚህም የሰው ልጅ ክቡር የሆነ ሕይወት ይመራ ዘንድ ግዴታ የሆነው ሚዛናዊነት ይረጋገጣል።››

ሮዝማሪ ሃው
እንግሊዛዊት ጋዜጠኛ

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am



## እምነትና ጭንቀት አይገናኙም

‹‹የውቅያኖስ ተለዋዋጭ ሞገዶች ታች ያለውን ጥልቁን ክፍል ጸጥታ ፈጽሞ አያደፈርስም፤ሰላሙንም አያናጋም። በአላህ ያለውን እምነቱን በእውነት ጥልቀት እንዲኖረው ያደረገ ሰውም እንደዚያ ነው። ለጭንቀት አይበገርም። ሚዛናዊነቱን የጠበቀ ነው። ቀናት ሊያመጡ የሚችሉትን ነገሮች ሁሉ ለመጋፈጥም ዘውትር ዝግጁ ነው።››

**ዊልያም ጀምስ**

**አሜሪካዊ ፈላስፋ**

አደጋ የማይጎትቱት ስለመሆኑ ዋስትና የሚሰጥ ምንም ነገር የለም። ሁለተኛ፦ ኢማን ከደስተኝነት አበይት መስፈርቶች ሁለቱን ማለትም ውስጣዊ መረጋጋትና የልብ እፎይታን የሚሰጥ መሆኑ ነው። በችግሮችና በቀውሶች ማዕበል ሲናወጡ መዳኛና መጠጊያው ኢማን ብቻ ነው። ኢማን በሌለበት የፍርሃትና የጭንቀት መንስኤዎች እየጨመሩ ይሄዳሉ። ከኢማን ጋር ግን ከአላህ (ሱ.ወ.) በስተቀር ሊፈሩት የሚገባ አንዳች ነገር አይኖርም።

አማኝ የሆነ ልብ፣በአላህ ላይ የሚተማመን በመሆኑ ማንኛውንም አስቸጋሪ ሁኔታ አቅልሎ ይመለከታል። ከኢማን የተራቆተ ልብ ግን ከዛፉ እንደ ረገፈ ቅጠል በነፋስ ወዲያና ወዲህ የሚላጋ ይሆናል። ከሞትና ይህችን ዓለም ለቆ ከመሰናበት ይበልጥ ሰውን የሚያስፈራ ምን ነገር ይኖራል?! በአማኝ ሰው ዘንድ ግን ሞት የመረጋጋት መንስኤ እንጂ የፍርሃት መነሻ አይደለም። ልቡ በኢማንና በአላህ ፍራቻ (በተቅዋ) ለተሞላ ሰው ሞት ምኑም አይደለም!!

ኢማን በሰው ልጅ የሰራ አካላት የሰላም የደህንነትና የመረጋጋት ስሜትን ይዘራል። አማኝ ሰው፣እውነተኛ እምነቱ የአላህን ረድኤት፣ጥበቃውንና እንክብካቤውን በተስፋ የመጠበቅ የማያቋርጥ ስንቅ ስለሚያቀርብለት፣ደህንነት የሚሰማውና የተረጋጋ ሆኖ ነው በአላህ መንገድ የሚጓዘው። ምንጊዜም አላህ (ሱ.ወ.) በረድኤቱና በእገዛው ከርሱ መሆኑ ይሰማዋል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَأَنَّ ٱللَّهَ مَعَ ٱلْمُؤْمِنِينَ ﴿١٩﴾}[الأنفال: ١٩]

‹‹አላህም ከምእመናን ጋር ነው።››[አል አንፋል፡19]

አማኝ ሰው የፈለገ ዓይነት ችግር ቢደርስበት፣የፈለገ ፈተና ቢያጋጥመው፣በአንጸባራቂ ብርሃን ያሸበረቁ የአላህ መጽሐፍና ቃሎቹ፣የነፍስያውን ጉትጎታና የአካላቱን ሕመም ለማስወገድ ዋስትናው ናቸው። እናም ፍርሃትና ስጋቱ በሰላምና መረጋጋት ይለወጣል። ዕድለ ቢስነትና ጭንቀቱ በተድላና በደስተኝነት ይቀየራል። በመሆኑም የምድር ሀብት በሙሉ ቢሰጠው እንኳ ሊያገኝ የማይችለውን ስነልቦናዊና መንፈሳዊ ደስተኝነት ወደሚያጎናጽፈው እፎይታ ይመራዋል።

## 5- ከዱንያ ሕይወት ወደ መደሰቻ ጀነት የሚደረግ የደስተኝነት ጉዞ፦


የሰዎች ሕይወት ሦስት እርከኖች እንዳሉት ይታወቃል። አንደኛው የዱንያ ሕይወቱ፣ሁለተኛው ከሞተ በኋላ የሚጀምረው የመቃብር ሕይወቱ፣ሦስተኛው የትንሳኤ ቀን ሕይወቱ ናቸው። የደስተኝነትና የመታደል መንገድም በነዚህ ሁሉ እርከኖች ውስጥ ያልፋል። የዱንያውን አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{مَنْ عَمِلَ صَٰلِحًا مِّن ذَكَرٍ أَوْ أُنثَىٰ وَهُوَ مُؤْمِنٌ فَلَنُحْيِيَنَّهُۥ حَيَوٰةً طَيِّبَةً وَلَنَجْزِيَنَّهُمْ أَجْرَهُم بِأَحْسَنِ مَا كَانُوا۟ يَعْمَلُونَ ﴿٩٧﴾}[النحل: ٩٧]

‹‹ከወንድ ወይም ከሴት፣እርሱ አማኝ ኾኖ በጎን የሠራ፣መልካም ኑሮን በእርግጥ እናኖረዋለን፤ይሠሩትም ከነበሩት ነገር በመልካሙ ምንዳቸውን እንመነዳቸዋለን።››[አል ነሕል፡97]

ይህም ሀብትና ንብረቱ ትንሽ ቢሆን እንኳ፣በመንፈስ እርካታ፣በሕሊና እፎይታ፣በውስጣዊ ሰላምና መረጋጋት፣በአላህ ላይ በሚኖረው መተማመንና በእርግጠኝነቱ አማካይነት፣ በዚህች ዓለም ሕይወቱ ደስተኛ የሆነ የተረጋጋ ሕይወት እንዲኖር እናደርጋለን ማለት ነው። አማኙ በመቃብር ሕይወቱ የሚያገኘውን ደስተኝነት በተመለከተ ደግሞ አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ.) ከአላህ መልክተኛ ﷺ በስተላለፉት ተከታዩ ሐዲስ ውስጥ እናገኛለን፦ ‹‹ ሙእምን ሰው መቃብሩ ውስጥ በእርግጥ ለምለም ጨፌ ውስጥ ነው፤በመቃብሩ ውስጥ ሰባ ክንድ ይሰፋለታል፤እንደ ሙሉ ጨረቃም ይበራለታል።›› [አልባኒ ‹ሐስን› ብሎታል]


## የመዳኛ ወደብ




‹‹አንድ ሙስሊም ቁርኣንን በጥልቀት ባነበበና፣እስላማዊ የዕባዳ ግዴታዎችን በሐቀኝነት በፈጸመ ቁጥር፣በእስላም ጉዞው ወደ መዳኛው አስተማማኝ ወደብ ያመራል። በመረጋጋትና በእርካታ ባቡር ይሳፈርና የሰይጣን ተንኮል ከርሱ ይርቃል።››

**ከሽየስ ክላይ**

**አሜሪካዊ ቦክሰኛ**




## የዛሬው ዓለምና የወዲያኛው ዓለም ሕይወት ሃይማኖት



‹‹ዐዋቂ የሆነ ሰው በተፈጥሮው ወደ እስላም ያዘነብላል:: [እስላም] የዚህን ዓለም ሕይወትና የወዲያኛውን ዓለም ሕይወት ጉዳዮችን እኩል አድርጎ የሚመለከት ብቸኛው ሃይማኖት ነውና::››

**በርናንድ ሾው**

**እንግሊዛዊ ጸሐፊ**



በወዲያኛው የኣኼራ ዘላለማዊ ሕይወቱ የሚጠብቀውን መታደልና ደስተኘነት በተመለከተ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَأَمَّا ٱلَّذِينَ سُعِدُواْ فَفِى ٱلْجَنَّةِ خَٰلِدِينَ فِيهَا مَا دَامَتِ ٱلسَّمَٰوَٰتُ وَٱلْأَرْضُ إِلَّا مَا شَآءَ رَبُّكَ ۖ عَطَآءً غَيْرَ مَجْذُوذٍ ﴿١٠٨﴾} [هود: ١٠٨]

‹‹እነዚያም ዕድለኞቹማ ጌታህ ከሻው (ጭማሬ) ሌላ፣ሰማያትና ምድር እስከ ዘወተሩ ድረስ፣በውስጧ ዘውታሪዎች ኾነው በገነት ውስጥ ይኖራሉ፤የማይቋረጥ ስጦታን ተሰጡ::››[ሁድ:108]

በዚህች ዓለማዊ ሕይወት ደስተኘነትን ሲታደሉ፣በመጭው የኣኼራ ዘላለማዊ ሕይወት ደግሞ መታደልን ተቀዳጅተዋል::

ስለዚህም እስላም ለሰው ልጅ ዘላለማዊ የሆነ ደስተኘነትንና መታደልን፣ዛሬ ለሚኖረው ሕይወቱ ደስተኘነትን፣በወዲያኛው የኣኼራ ሕወቱም መታደልን ይዞለት ነው የመጣው:: አላህ ዘንድ ያለው በላጭና ዘላለማዊ ነውና:: ይህም ብቻ ሳይሆን አላህ (ሱ.ወ.) የዱንያንና የኣኼራን ደስተኘነትና መታደል፣በመካከላቸው ግጭትና ቅራኔ ሳይኖር የተሳሰሩና የተቆራኙ አድርጓቸዋል:: ይህች የዱንያ ሕይወት ወደ ኣኼራና በትንሣኤው ቀንም ወደ ታላቁ መታደልና ደስታ የምታደርስ መንገድ ነች:: የዘላለማዊ መታደልና የደስተኘነት መንገድ በዱንያም ሆነ በኣኼራ አንድ መንገድ ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{مَّن كَانَ يُرِيدُ ثَوَابَ ٱلدُّنْيَا فَعِندَ ٱللَّهِ ثَوَابُ ٱلدُّنْيَا وَٱلْـَٔاخِرَةِ ۚ وَكَانَ ٱللَّهُ سَمِيعًۢا بَصِيرًا ﴿١٣٤﴾} [النساء: ١٣٤]

‹‹የቅርቢቱን ዓለም ምንዳ የሚፈልግ የኾነ ሰው፣አላህ ዘንድ የቅርቢቱና የመጨረሻይቱ ምንዳ አለለ:: አላህም ሰሚ ተመልካች ነው::››[አል ኒሳእ: 134]



## በቅርቢቱ ሕይወት ለደስተኘነት የሚያበቁ መረማመጃዎች በእስላም፦

ዛሬ በምንኖረው ሕይወት ለመታደልና ደስተኘነትን ለማግኘት በእስላም ውስጥ በርካታ መረማመጃዎችና ምክንያቶች ይገኛሉ:: ከነዚህም መካከል፦

### 1- በተውሒድና በአላህ በማመን የሚገኝ ደስተኘነት፦

ተውሒድ የሚያስገኘውን እፎይታ የሚመስል እፎይታ፣ተውሒድ የሚያላብሰውን ውስጣዊ መረጋጋት የመሰለ ውስጣዊ መረጋጋትም የለም:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَلَمْ يَلْبِسُوٓاْ إِيمَٰنَهُم بِظُلْمٍ أُوْلَٰٓئِكَ لَهُمُ ٱلْأَمْنُ وَهُم مُّهْتَدُونَ ﴿٨٢﴾} [الأنعام: ٨٢]

‹‹እነዚያ ያመኑና እምነታቸውን በበደል ያልቀላቀሉ፣እነዚያ ለነርሱ ጸጥታ አላቸው፤እነሱም የተመሩ ናቸው::››[አል አንዓም: 82]

እናም በሚኖረን የተውሒድ ምሉእነት ደረጃና መጠንም በዱንያና በኣኼራም መድህንና መረጋጋትን፣መታደልና ደስተኘነትን እናገኛለን:: አላህ (ሱ.ወ.) በተውሒዱ ልክ የባለቤቱን ልብ የሚያሰፋና ደስተኘነትን የሚያስገባበት ሲሆን፣አላህ ይጠብቀንና ሽርክ ደግሞ በባለቤቱ ላይ ወደ ከፍታ ቦታ የሚወጣ ሰውን እንደሚያጋጥመው ዓይነት የልብ ጥበንና ጭንቀት ያስከትልበታል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{فَمَن يُرِدِ ٱللَّهُ أَن يَهْدِيَهُۥ يَشْرَحْ صَدْرَهُۥ لِلْإِسْلَٰمِ ۖ وَمَن يُرِدْ أَن يُضِلَّهُۥ يَجْعَلْ صَدْرَهُۥ ضَيِّقًا حَرَجًا كَأَنَّمَا يَصَّعَّدُ فِى ٱلسَّمَآءِ ۚ كَذَٰلِكَ يَجْعَلُ ٱللَّهُ ٱلرِّجْسَ عَلَى ٱلَّذِينَ لَا يُؤْمِنُونَ ﴿١٢٥﴾} [الأنعام: ١٢٥]



### ውስብስብነት የሌለው ዐቂዳ

‹‹የእስላም እምነት (ዐቂዳ)፣በርሱ ማመን በሁሉም ዓይነት ግራ መጋባት፣ስጋትና ፍርሃት ላይ መንገድ የሚዘጋ፣በያንዳንዱ ነፍስ ውስጥ መረጋጋትን የሚዘራ ቀለል ያለ አንድ እምነት ነው:: የዚህ እምነት በርም ለማንም ሰው ክፍት ነው:: በዜግነቱ ወይም በቆዳ ቀለሙ ምክንያት ማንም ሰው ከርሱ አይከለከልም:: በዚህ መልኩም እያንዳንዱ ሰው፣በእኩልነት፣የዓለማትን ጌታ አላህን በመፍራት ደረጃ ካልሆነ በስተቀር ማንም በማይበላለጥበት ፍትሐዊ የእኩልነት መሰረት ላይ በቆመው በዚህ መለኮታዊ እምነት ጥላ ስር ቦታውን ያገኛል::››

**ነዝሚ ሉቃ**

**ግብጻዊ ፈላስፋና አሳቢ**



https://www.path-2-happiness.com/am

‹‹አላህም ሊመራው የሚሻውን ሰው፣ደረቱን (ልቡን) ለእስላም ይከፍትለታል፤ሊያጠመውም የሚሻውን ሰው፣ደረቱን ጠባብ፣ቸጋራ፣ወደ ሰማይ ለመውጣት እንደሚታገል፣ያደርገዋል። እንደዚሁ አላህ በነዚያ በማያምኑት ላይ ርክሰትን ያደርጋል።››[አል አንዓም:125]

አላህ (ሱ.ወ.) ልቡን ለእስላም አስፍቶለት ከርሱ ዘንድ የሆነ ብርሃን የፈነጠቀለት ሰውና፤ በሽርክና፣በጣዖታዊነት፣በግልጽ ጥመትና አላህን (ሱ.ወ.) በመርሳት ጽልመት ውስጥ የሚዳክር ሰው ፈጽሞ እኩል አይደሉም። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{أَفَمَن شَرَحَ ٱللَّهُ صَدۡرَهُۥ لِلۡإِسۡلَٰمِ فَهُوَ عَلَىٰ نُورٖ مِّن رَّبِّهِۦۚ فَوَيۡلٞ لِّلۡقَٰسِيَةِ قُلُوبُهُم مِّن ذِكۡرِ ٱللَّهِۚ أُوْلَٰٓئِكَ فِي ضَلَٰلٖ مُّبِينٍ ﴿٢٢﴾}[الزمر: ٢٢]

‹‹አላህ ደረቱን ለእስላም ያሰፋለትና እርሱም ከጌታው ዘንድ በብርሃን ላይ የኾነ ሰው፣(ልቡ እንደ ደረቀ ሰው ነውን?) ልቦቻቸውም ከአላህ መውሳት ለደረቁ ሰዎች ወዮላቸው፤እነዚያ በግልጽ መሳሳት ውስጥ ናቸው።››[አል ዙመር:22]

በሽርክ ጨለማ ውስጥ ሙት የነበረና አላህ (ሱ.ወ.) በቸርነቱ በእዝነቱ በተውሒድ ሕያው ያደረገው ሰው፣ፈጽሞ በማይወጣ ሁኔታ በሽርክ ጨለማ ውስጥ ሰምጦ እንደቀረ ሰው አይደለም። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{أَوَ مَن كَانَ مَيۡتٗا فَأَحۡيَيۡنَٰهُ وَجَعَلۡنَا لَهُۥ نُورٗا يَمۡشِي بِهِۦ فِي ٱلنَّاسِ كَمَن مَّثَلُهُۥ فِي ٱلظُّلُمَٰتِ لَيۡسَ بِخَارِجٖ مِّنۡهَاۚ كَذَٰلِكَ زُيِّنَ لِلۡكَٰفِرِينَ مَا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ﴿١٢٢﴾}[الأنعام: ١٢٢]

‹‹ሙት የነበረና ሕያው ያደረግነው፣ለርሱም በሰዎች መካከል በርሱ የሚኼድበትን ብርሃን ያደረግንለት ሰው፣በጨለማዎች ውስጥ ከርሷ የማይወጣ ኾኖ እንዳለለ ሰው ብጤ ነውን? እንደዚሁ ለከሃዲዎች ይሠሩት የነበሩት ነገር ተጌጠላቸው።››[አል አንዓም:122]

## 2- የአላህ (ሱ.ወ.) ውዳሴ፣እርሱን መማጸንና ወደርሱ መቃረብ፦



የሰው ልጅ የፈለገውን ያህል ዓለማዊ መጠቀሚያና መደሰቻ ቢሰጠው፣ያሻውን ያህል የመደሰቻና የእርካታ ማግኛ መንገዶችን ቢታደል፣ከአላህ (ሱ.ወ.) መንገድ የራቀ እስከሆነ ድረስ እውነተኛውን ደስተኝነት ማግኘት አይችልም። እውነተኛ ደስተኝነትና እርካታ ማግኘት የሚችለው ወደ አላህ (ሱ.ወ.) ሲቀርብ፣በውዳሴው ጥላ ስርና በርሱ አፀድ ውስጥ ሲሆን ብቻ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَتَطۡمَئِنُّ قُلُوبُهُم بِذِكۡرِ ٱللَّهِۗ أَلَا بِذِكۡرِ ٱللَّهِ تَطۡمَئِنُّ ٱلۡقُلُوبُ ﴿٢٨﴾}[الرعد: ٢٨]

‹‹(እነሱም) እነዚያ ያመኑ፣ልቦቻቸውም አላህን በማውሳት የሚረኩ ናቸው፤ንቁ አላህን በማውሳት ልቦች ይረካሉ።››[አል ረዕድ:28]

ለምን ቢባል፦ ‹‹ልብ ውስጥ ወደ አላህ (ሱ.ወ.) ፊትን መመለስ ብቻ የሚያሰባስበው መዋለል ይገኛል። ለብቻው ገለል ሲልም በርሱ መጽናናት ብቻ የሚያስወግደው ብቸኝነትና መቦዘንም አለበት። እርሱን የማወቅና በፍጹምነት እርሱን የመገዛት ደስተኝነት ብቻ የሚያስወግደው ሐዘንም ይገኝበታል። ወደርሱ መሰባሰብና ከርሱ ወደርሱ መሸሽ ብቻ የሚያረጋጋው ጭንቀትም አለበት። ትእዛዙን፣እገዳውንና ውሳኔውን ወደ መቀበልና ከርሱ ጋር እስከሚገናኝበት ጊዜ ድረስ በዚያ ላይ መታገስ ብቻ የሚያጠፋው የቁጭት እሳትም አለበት። ተፈላጊው እርሱ ብቻ እስኪሆን ድረስ የማይገታ ብርቱ ፍላጎትም አለበት። በርሱ ፍቅር፣ወደርሱ በመመለስ፣ዘውትር እርሱን በማውሳትና በእርግጠኝነት ለርሱ ፍጹም በመሆን ብቻ የሚሸፈን እጦትም ይገኝበታል፤ዱንያና በርሷ ውስጥ ያለው ሁሉ ቢሰጠው እንኳ ያንን እጦት ፈጽሞ መሸፈን አይችልም።››[1]


## 3- መልካም ሥራ፦

አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ طُوبَىٰ لَهُمۡ وَحُسۡنُ مَـَٔابٖ ﴿٢٩﴾} [الرعد: ٢٩]

‹‹እነዚ ያመኑትና መልካም ሥራዎችን የሠሩት፣ለነሱ ደግ ኑሮ፣መልካም መመለሻም አላቸው።››[አል ረዕድ:29]

(1) እብን አልቀይም፣መዳሪጅ አስሳሊኪን፣ገጽ 743





https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am



**እውነተኛው ደህንነት**

‹‹ሙስሊሞች በሚስግዱበት ጊዜ የሚሰማቸው ስሜት ይሰማኛል፦ ጥዑም ቅንጅት፣በደስታ መፍነክነክ:: ይህ ልጆቼ በሰላም መሆናቸውን ያወቅሁ ያህል እየተኩራራሁ ይሰማኝ የነበረው ስሜት ነው:: በእርግጥ ከዚህ በላይ ማለት አልፈልግም::››

**ሎራን ቡሥ**
**እንግሊዛዊት የሕግ ባለሞያ**

እነዚያ ከልቦቻቸው በአላህ፣በመላእኮቹ፣በመጽሐፎቹ፣በመልክተኞቹና በመጨረሻው ቀን ያመኑና ይህን እምነት በመልካም ሥራዎች ማለትም አላህን መውደድ፣እርሱን መፍራት፣እርሱን ብቻ ተስፋ ማድረግ በመሳሰሉ የልብ ሥራዎችና ሶላትን በመሳሰሉ አካላዊ ሥራዎች በተግባር ያረጋገጡ ሰዎች የተሟላ እፎይታና የተሟላ መረጋጋት ይታደላሉ:: ይህም በዱንያና በኣኼራ ሕይወታቸው ከአላህ (ሱ.ወ.) ውዴታና ከበሬታውን የተቸሩ በመሆናቸው ነው:: ስለዚህም ከኢማን ጋር በመልካም ሥራ ላይ መሰማራት ይኖርብናል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَٱلَّذِينَ هَادُواْ وَٱلصَّٰبِـُٔونَ وَٱلنَّصَٰرَىٰ مَنْ ءَامَنَ بِٱللَّهِ وَٱلْيَوْمِ ٱلْأَخِرِ وَعَمِلَ صَٰلِحًا فَلَا خَوْفٌ عَلَيْهِمْ وَلَا هُمْ يَحْزَنُونَ ٦٩}[المائدة: ٦٩]

‹‹እነዚያ ያመኑና እነዚያም ይሁዳውያን የኾኑ፣ሳቢያኖችም፣ ክርስቲያኖችም፣ (ከነርሱ) በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነና መልካምን ሥራ የሠራ ሰው፣በነርሱ ላይ ፍርሃት የለባቸውም፤እነርሱም አያዝኑም::››[አል ማእዳህ:69]

ነቢዩ ﷺ እርካታና እፎይታቸውን በሶላትና በአምልኮተ-አላህ (በእባዳ) ውስጥ ያገኙ የነበረ ሲሆን ይህንኑ በማስመልከት እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ቢላል ሆይ! ለሶላት የመጨረሻውን ጥሪ (እቃማህ) አድርግና በርሱ እፎይ አሰኘን፣አርካን::››

## 4- ልገሳ የደስተኝነት ምስጢር ነው፦

ይህ በተግባር የታየና የተረጋገጠ ጉዳይ ነው:: ለሌሎች በጎ የሚሠራ ሰው ከሰው ሁሉ ደስተኛ መሆኑና በምድር ላይ ከሌሎች ይበልጥ ተቀባይነት የሚቸረው ሰው መሆኑን እናውቃለን:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{لَن تَنَالُواْ ٱلْبِرَّ حَتَّىٰ تُنفِقُواْ مِمَّا تُحِبُّونَ وَمَا تُنفِقُواْ مِن شَيْءٍ فَإِنَّ ٱللَّهَ بِهِۦ عَلِيمٌ ٩٢}[آل عمران: ٩٢]

‹‹የምትወዱትን እስከምትለግሱ ድረስ በጎ ሥራን አታገኙም:: የምትለግሱትን ማንኛውንም ነገር፣አላህ ያውቀዋል::››[ኣሊ. ዒምራን:92]

ልገሳ የተለያዩ ገጽታዎች አሉት:: ገንዘብ መስጠትን አላህ (ሱ.ወ.) አንዱ የእስላም ማእዘን አድርጓ ከሀብታሙ ተወስዶ ለድሃው የሚከፈለውን ዘካ በግዴታነት ደንግጓል:: ይህ ልገሳም ጉራና መመጻደቅ በማይኖርበት ሁኔታ ለአላህ (ሱ.ወ.) ልቦናን ፍጹም በማድረግ ከሚወዱት ነገር እንዲሆንም ደንግጓል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تُبْطِلُواْ صَدَقَٰتِكُم بِٱلْمَنِّ وَٱلْأَذَىٰ}[البقرة: ٢٦٤]



‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! . . ምጽዋቶቻችሁን በመመጻደቅና በማስከፋት አታበላሹ::››[አል በቀራህ: 264]

ልገሳውም በገንዘብ ላይ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን ወደ ሁሉም ዓይነት ልገሳ በመስፋት ገንዘብን፣ምግብን፣ዕውቀትና ጉልበትንም ያጠቃልላል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَيُطْعِمُونَ ٱلطَّعَامَ عَلَىٰ حُبِّهِۦ مِسْكِينًا وَيَتِيمًا وَأَسِيرًا ٨ إِنَّمَا نُطْعِمُكُمْ لِوَجْهِ ٱللَّهِ لَا نُرِيدُ مِنكُمْ جَزَآءً وَلَا شُكُورًا ٩}[الإنسان: ٨- ٩]

‹‹ምግብንም፣ከመውደዳቸው ጋር ለድኻ፣ለየቲምም፣ለምርኮኛም፣ለእስረኛም ያበላሉ:: የምናበላችሁ ለአላህ ውዴታ ብቻ ነው፤ከናንተ ዋጋንም ማመስገንንም አንፈልግም::››[አል ደህር:8-9]

ምጽዋትና ልገሳ ሌላው ቀርቶ በፈገግታና በጥሩ ፊት ብቻ እንኳ ሊገለጽ ይችላል:: ነቢዩ ﷺ ፦ ‹‹ወንድምህን በፈካ ፊት በፈገግታ መቀበል ሶደቃ (ምጽዋት) ነው::›› [በትርምዚ የተዘገበ] ብለዋል:: በተጨማሪም ነቢዩ ﷺ ፦ ‹‹የወንድሙን ጉዳይ ለማሳካት የተሰማራን ሰው አላህ የርሱ ጉዳይ አስፈጻሚ ይሆንለታል:: ለአንድ ሙስሊም አንድን ችግር የፈታለት ሰው፣በዚያ ከትንሳኤው ቀን ችግሮች አንዱን ችግር ያስወግድለታል:: የአንድን ሙስሊም ገበና የሸፈነለትን ሰው፣አላህ በትንሳኤው ቀን ገበናውን ይሸፍንለታል::›› ብለዋል:: [በአቡ ዳውድ የተዘገበ] ይህ ልገሳ በዓለማዊ ሕይወትም ደስተኝነትን የሚያጎናጽፍ መሆኑ ጥርጥር የለውም:: አንዳች ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለጉራና ለመመጻደቅ የሚለገስ ከሆነ ግን መስሎ ቢታይ እንኳ ምንም ዓይነት ደስተኝነት አያስገኝም::

## 5- በአላህ (ሱ.ወ.) ላይ መመካት (ተወኩል) የደስተኝነት መክፈቻ ቁልፍ ነው፦

ሰው ብዙ ጊዜ አንድ ነገር ለማድረግ ፈልጎ የአቅም ማነስ ወይም ያለመቻል ስሜት ይጠናወተውና የፈለገውን ለማድረግ ይችል ዘንድ አቅም ባለውና በሚተማመንበት ሌላ ወገን መታገዝን አስፈላጊ ሆኖ ያገኛል:: ለዚህ ከአላህ (ሱ.ወ.) የበለጠ ብርቱ



https://www.path-2-happiness.com/am

ኃይልና ረዳኢ ከቶም የት አለና?! የሰማያትና የምድር ግዛት በእጁ ወደ ሆነው፣የሻውን ነገር የማድረግ ፍጹማዊ ሥልጣን የርሱ ብቻ ወደ ሆነው ኃያሉ ቻይ ጌታ ወደ አላህ መጠጋትና በርሱ ላይ መተማመን የደስተኝነት መክፈቻ ቁልፍ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّمَآ أَمۡرُهُۥٓ إِذَآ أَرَادَ شَيۡـًٔا أَن يَقُولَ لَهُۥ كُن فَيَكُونُ ٨٢} [يس: ٨٢]

‹‹ነገሩም፣አንዳችን በሻ ጊዜ፣ኹን ማለት ነው፤ወዲውኑ ይኾናልም።››[ያሲን:82]

ለዚህም ነው አላህ (ሱ.ወ.) በርሱ ላይ ብቻ እንድንተማመንና በርሱ ብቻ እንድንመካ ያዘዘን። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَعَلَى ٱللَّهِ فَتَوَكَّلُوٓاْ إِن كُنتُم مُّؤۡمِنِينَ ٢٣} [المائدة: ٢٣]

‹‹ምእመናንም እንደ ኾናችሁ በአላህ ላይ ተመኩ አሉ።››[አል ማእዳህ:23]

ከርሱ ወዲያ መተማመኛ የለም፤መጠጊያና መመኪያም በርሱ በቃ። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَتَوَكَّلۡ عَلَى ٱللَّهِۚ وَكَفَىٰ بِٱللَّهِ وَكِيلٗا ٨١} [النساء: ٨١]

‹‹በአላህም ላይ ተጠጋ፤መጠጊያም በአላህ በቃ።››[አል ኒሳእ:81]

ይህን ማድረግ ያለ ጥርጥር እርካታን፣እፎይታን፣መረጋጋትን፣መብቃቃትን፣ደስተኝነትንና ሞክረው ያዩት ብቻ የሚያውቁትን ስኬታማነት ያስጨብጣል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَن يَتَّقِ ٱللَّهَ يَجۡعَل لَّهُۥ مَخۡرَجٗا ٢ وَيَرۡزُقۡهُ مِنۡ حَيۡثُ لَا يَحۡتَسِبُۚ وَمَن يَتَوَكَّلۡ عَلَى ٱللَّهِ فَهُوَ حَسۡبُهُۥٓۚ إِنَّ ٱللَّهَ بَٰلِغُ أَمۡرِهِۦۚ قَدۡ جَعَلَ ٱللَّهُ لِكُلِّ شَيۡءٖ قَدۡرٗا ٣} [الطلاق: ٢-٣]

‹‹አላህንም የሚፈራ ሰው፣ለርሱ መውጫን ያደርግለታል። ከማያስበውም በኩል ሲሳይን ይሰጠዋል፤በአላህም ላይ የሚጠጋ ሰው፣እርሱ በቂው ነው፤አላህ ፈቃዱን አድራሽ ነው፤አላህ ለነገሩ ሁሉ የተወሰነ ጊዜን በእርግጥ አድርጓል።››[አል ጦላቅ:2-3]





ተወኩል በተጨማሪም ከተረገመው ሰይጣን በአላህ (ሱ.ወ.) መጠበቅንም ያስገኛል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّهُۥ لَيۡسَ لَهُۥ سُلۡطَٰنٌ عَلَى ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَلَىٰ رَبِّهِمۡ يَتَوَكَّلُونَ ٩٩} [النحل: ٩٩]

‹‹እርሱ በነዚያ ባመኑትና በጌታቸው ላይ በሚጠጉት ላይ ለርሱ ሥልጣን የለውምና።››[አል ነሕል:99]

ከጠላት ጥቃትም ይከላከላል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ٱلَّذِينَ قَالَ لَهُمُ ٱلنَّاسُ إِنَّ ٱلنَّاسَ قَدۡ جَمَعُواْ لَكُمۡ فَٱخۡشَوۡهُمۡ فَزَادَهُمۡ إِيمَٰنٗا وَقَالُواْ حَسۡبُنَا ٱللَّهُ وَنِعۡمَ ٱلۡوَكِيلُ ١٧٣ فَٱنقَلَبُواْ بِنِعۡمَةٖ مِّنَ ٱللَّهِ وَفَضۡلٖ لَّمۡ يَمۡسَسۡهُمۡ سُوٓءٞ وَٱتَّبَعُواْ رِضۡوَٰنَ ٱللَّهِۗ وَٱللَّهُ ذُو فَضۡلٍ عَظِيمٍ ١٧٤ إِنَّمَا ذَٰلِكُمُ ٱلشَّيۡطَٰنُ يُخَوِّفُ أَوۡلِيَآءَهُۥ فَلَا تَخَافُوهُمۡ وَخَافُونِ إِن كُنتُم مُّؤۡمِنِينَ ١٧٥} [آل عمران: ١٧٣-١٧٥]

‹‹እነዚያ ሰዎቹ ለነርሱ፦ ሰዎች ለናንተ (ጦርን) አከማችተዋልና ፍሩዋቸው ያሉዋቸውና (ይህም) እምነትን የጨመረላቸው፣በቂያችንም አላህ ነው፣ምን ያምርም መጠጊያ! ያሉ ናቸው። ከአላህም በኾነ ጸጋና ችሮታ ክፉ ነገር ያልነካቸው ኾነው ተመለሱ፤የአላህንም ውዴታ ተከተተሉ፤አላህም የታላቅ ችሮታ ባለቤት ነው። ይሃችሁ፣ሰይጣን ብቻ ነው፣ወዳጆቹን ያስፈራራችኋል፤አትፍሩዋቸውም፤ምእመናንም እንደኾናችሁ ፍሩኝ።›› [ኣሊ ዒምራን:173-175]

የተወኩል ምስጢርና እውነታው የልብ በአላህ ላይ ብቻ መተማመንና በርሱ

‹‹ሌሎችን መርዳት የስነልቦና ውጥረትን እንደሚፈውስ የሚያረጋግጡ ሳይንሳዊ ጥናቶች አሉ። በስነልቦና መስክ ኤክስፐርት የሆኑ ሰዎች እንዳረጋገጡት፣አንድ ሰው ሌሎችን መርዳት የነርቭ ውጥረትን ይቀንሳል። ይኸውም በሌሎች እገዛ ላይ መሰማራት ‹እንዶርፊን› የተባለ ሆርሞንን መመንጨት የሚያፋጥን ሲሆን ሆርሞኑ የደስተኝነት ስሜትና ንቃት እንዲሰማ የሚያጋዝ ነው። አሜሪካ የሚገኘው ‹ጤንነትን የማላቅ›› ተቋም የቀድሞ ዳይሬክተር አለን ሌክስ፣አንድ ሰው ሌሎችን ሲረዳ ስለ ግላዊ ጭንቀቶቹና ውጥረቶቹ ማሰቡን የሚቀንስ በመሆኑና በዚህም የመንፈስ እርካታ የሚሰማው በመሆኑ፣ሌሎችን መርዳት የነርቭ ውጥረትን እንሚያላላ ያረጋግጣሉ።››

https://www.path-2-happiness.com/am

ብቻ መመካት ነው። ልቡ ከርሱ በስተቀር በሌላ ላይ ከመተማመንና ከመጠጋት የጸዳ እስከሆነ ድረስ ውጤትን ከሳቢያ ለመጠበቅ መረማመጃ ምክንያቶችን (አስባብ) ሁሉ መጠቀም ጉዳት አያስከትልበትም። በተመሳሳይ መልኩም ልቡ በሌላ ላይ እየተንጠላጠለ፣በሌላ እየተመካና ወደ ሌላ እየተጠጋ በአንደበቱ ‹‹ተወከልቱ ዐለልኳህ››፣በአላህ ላይ እተማመናለሁ ማለቱ ምንም አይጠቅመውም። በምላስ መተማመንና በልብ መተማመን የተለያዩ ነገሮች ናቸውና።

## 6- ደስተኝነት በእርግጠኝነት (የቂን) እና በአላህ ላይ በመተማመን ውስጥ ነው፦

ኢማን ለአማኙ ሰው እርግጠኝነትንና ሙሉ በሙሉ በአላህ (ሱ.ወ.) ላይ መተማመንን እውን ያደርግለታል። ይህም በራስ መተማመንን ስለሚያላብሰውና ነገሩ ሁሉ በአላህ (ሱ.ወ.) እጅ መሆኑን ስለሚረዳ በዚህ ሕይወቱ ውስጥ ምንም ነገር አያሰጋውም። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِن يَمۡسَسۡكَ ٱللَّهُ بِضُرّٖ فَلَا كَاشِفَ لَهُۥٓ إِلَّا هُوَۖ وَإِن يَمۡسَسۡكَ بِخَيۡرٖ فَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٞ ﴿١٧﴾}[الأنعام: ١٧]

‹‹አላህም በጉዳት ቢነካህ፣ለርሱ (ለጉዳቱ) ከርሱ በቀር ሌላ አስወጋጅ የለም፤በበጎም ነገር ቢነካህ እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው፡፡››[አል አንዓም፡17]

ሙእምን ሰው፣ለርሱ የተጻፈው ሲሳይም በአላህ (ሱ.ወ.) እጅ ውስጥ ብቻ መሆኑንም በእርግጠኝነት ይገነዘባል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّمَا تَعۡبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ أَوۡثَٰنٗا وَتَخۡلُقُونَ إِفۡكًاۚ إِنَّ ٱلَّذِينَ تَعۡبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ لَا يَمۡلِكُونَ لَكُمۡ رِزۡقٗا فَٱبۡتَغُواْ عِندَ ٱللَّهِ ٱلرِّزۡقَ وَٱعۡبُدُوهُ وَٱشۡكُرُواْ لَهُۥٓۖ إِلَيۡهِ تُرۡجَعُونَ ﴿١٧﴾} [العنكبوت: ١٧]

‹‹ከአላህ ሌላ የምትግገዙት፣ጣዖታትን ብቻ ነው፤ውሸትንም ትቀጣጥፉላችሁ፤እነዚያ ከአላህ ሌላ የምትግገዟቸው ለናንተ ሲሳይን ሊሰጧችሁ አይችሉም፤ስለዚህ ሲሳይን ከአላህ ዘንድ ብቻ ፈልጉ፤ተገዙትም፤ለርሱም አመስግኑ፤ወደርሱ ትመለሳላችሁ፡፡››[አል ዐንከቡት፡17]

በምድር ላይ የሚንቀሳቀስ ማንኛውንም ፍጥረት የመመገብ ዋስትናን አላህ (ሱ.ወ.) ለራሱ ወስዷል። አላህ



https://www.path-2-happiness.com/am

(ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَا مِن دَآبَّةٖ فِي ٱلۡأَرۡضِ إِلَّا عَلَى ٱللَّهِ رِزۡقُهَا وَيَعۡلَمُ مُسۡتَقَرَّهَا وَمُسۡتَوۡدَعَهَاۚ كُلّٞ فِي كِتَٰبٖ مُّبِينٖ ﴿٦﴾} [هود: ٦]

‹‹በምድርም ላይ ምንም ተንቀሳቃሽ የለችም፣ምግቧ በአላህ ላይ ቢኾን እንጂ፤ማረፊያዋንም፣መርጊያዋንም፣ያውቃል፤ሁሉም ግልጽ በኾነው መጽሐፍ ውስጥ ነው፡፡››[ሁድ፡6]

ምግቡን ራሱ ተሸክሞ ማምጣት የማይችል ፍጥረት ቢሆን እንኳ አላህ (ሱ.ወ.) ይመግበዋል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَكَأَيِّن مِّن دَآبَّةٖ لَّا تَحۡمِلُ رِزۡقَهَا ٱللَّهُ يَرۡزُقُهَا وَإِيَّاكُمۡۚ وَهُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡعَلِيمُ ﴿٦٠﴾}[العنكبوت: ٦٠]

‹‹ከተንቀሳቃሽም ምግቧን ለመሸከም የማትችለው ብዙ ናት፣አላህ ይመግባታል፤እናንተንም፣(ይመግባል)፤እርሱ ሰሚው ዐዋቂው ነውና፡፡››[አል ዐንከቡት፡60]

ለርሱ የተመደበው ሲሳይ የግድ የሚመጣለት መሆኑንና ይህም ምንም ጥርጣሬ የሌለበት እውነት ስለመሆኑም እርግጠኛ ይሆናል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَفِي ٱلسَّمَآءِ رِزۡقُكُمۡ وَمَا تُوعَدُونَ ﴿٢٢﴾ فَوَرَبِّ ٱلسَّمَآءِ وَٱلۡأَرۡضِ إِنَّهُۥ لَحَقّٞ مِّثۡلَ مَآ أَنَّكُمۡ تَنطِقُونَ ﴿٢٣﴾}[الذاريات: ٢٢-٢٣]

‹‹ሲሳያችሁም፣የምትቀጠሩትም (ፍዳና ምንዳ) በሰማይ ውስጥ ነው። በሰማይና በምድር ጌታም እምላለሁ፣እርሱ እናንተ እንደምትናገሩት ብጤ እርግጠኛ ነው፡፡››[አል ዛርያት፡23]

አላህ (ሱ.ወ.) ሲሳይን ለሰዎች ሁሉ ወስኖና መጥኖ የከፋፈለላቸው መሆኑንም በእርግጠኝነት ይገነዘባል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قُلۡ إِنَّ رَبِّي يَبۡسُطُ ٱلرِّزۡقَ لِمَن يَشَآءُ وَيَقۡدِرُ وَلَٰكِنَّ أَكۡثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعۡلَمُونَ ﴿٣٦﴾}[سبأ: ٣٦]

‹‹በላቸው፦ ጌታዬ ሲሳይን ለሚሻው ሰው ያሰፋል፤ያጠባልም፤ግን አብዛኞዎቹ ሰዎች አያውቁም፡፡››[ሰበእ፡36]

አላህ (ሱ.ወ.) ሁሌም በጥሩውና በመጥፎውም የሚፈትነው መሆኑንም የማያወላውልና የጸና እምነት ያምናል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{كُلُّ نَفۡسٖ ذَآئِقَةُ ٱلۡمَوۡتِۗ وَنَبۡلُوكُم بِٱلشَّرِّ وَٱلۡخَيۡرِ فِتۡنَةٗۖ وَإِلَيۡنَا تُرۡجَعُونَ ﴿٣٥﴾}[الأنبياء: ٣٥]

‹‹ነፍስ ሁሉ ሞትን ቀማሽ ናት፤ለመፈተንም በክፉም በበጎም እንሞክራችኋለን፤ወደኛም ትመለሳላችሁ፡፡››[አል አንቢያ፡35]

የአላህ (ሱ.ወ.) ርህራሄና እዝነቱ ባይኖር ኖሮ በአስከፊ ሁኔታ እንደሚጠፋም ይረዳል።

ዕድሜው ረዘመም አጠረ፣በዚህች ዓለም ላይ ተላላፊ እንግዳ መሆኑን፣ያለ አንዳች ጥርጥር ወደ ወዲያኛው ዓለም እንደሚሸጋገርም ያውቃል። ስለዚህም በዚህ ዓለም ላይ ሕይወቱን የሚመራው ከዚህ መሰረታዊ መርህ በመነሳት ነው።



የኑሮ ውጣ ውረዶችን አይፈራም፤ጠላቱ በአንድ ክንድ ወይም ከዚያ ባነሰ ርቀት ወደርሱ የቀረበ ቢሆን እንኳ ከአላህ (ሱ.ወ.) በስተቀር ማንንም አይፈራም፡፡ ፈርዖንና ሰራዊቱ ወደ ነቢዩ ሙሳ عليه السلام የደረሱበትን ቅጽበት አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{فَلَمَّا تَرَٰٓءَا ٱلْجَمْعَانِ قَالَ أَصْحَٰبُ مُوسَىٰٓ إِنَّا لَمُدْرَكُونَ ﴿٦١﴾ قَالَ كَلَّآ ۖ إِنَّ مَعِىَ رَبِّى سَيَهْدِينِ ﴿٦٢﴾ فَأَوْحَيْنَآ إِلَىٰ مُوسَىٰٓ أَنِ ٱضْرِب بِّعَصَاكَ ٱلْبَحْرَ ۖ فَٱنفَلَقَ فَكَانَ كُلُّ فِرْقٍ كَٱلطَّوْدِ ٱلْعَظِيمِ ﴿٦٣﴾ وَأَزْلَفْنَا ثَمَّ ٱلْءَاخَرِينَ ﴿٦٤﴾ وَأَنجَيْنَا مُوسَىٰ وَمَن مَّعَهُۥٓ أَجْمَعِينَ ﴿٦٥﴾ ثُمَّ أَغْرَقْنَا ٱلْءَاخَرِينَ ﴿٦٦﴾ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَةً ۖ وَمَا كَانَ أَكْثَرُهُم مُّؤْمِنِينَ ﴿٦٧﴾} [الشعراء: ٦١- ٦٧]

‹‹ሁለቱ ጭፍሮችም በተያዩ ጊዜ፣የሙሳ ጓዶች እኛ (የፈርዖን ሰዎች) የሚደርሱብን ነን፣አሉ፡፡ (ሙሳ)፦ ተውዉ! ጌታዬ ከኔ ጋር ነው፤በእርግጥ ይመራኛል አለ፡፡ ‹‹ወደ ሙሳም ባሕሩን በበትርህ ምታው ስንል ላክንበት፣(መታውና) ተከፈለም፤ክፍሉም ሁሉ እንደ ታላቅ ጋራ ኾነ፡፡ እዚያም ዘንድ ሌሎችን አቀረብን፡፡ ሙሳንና ከርሱ ጋር ያሉትንም ሰዎች፣ሁሉንም አዳን፡፡ ከዚያም ሌሎቹን አሰጠምን፡፡ በዚህ ውስጥ ታላቅ ታምር አለበት፤አብዛኞቻቸውም አማኞች አልነበሩም፡፡››[አል ሹዐራ:61-67]

የእርግጠኞች ሁሉ ቁንጮ የሆኑት ሙሐመድ ﷺ ጠላታቸው ወደ እግሮቹ ቢመለከት ሊያገኛቸው በሚችልበት ሁኔታ ውስጥ ሆነው፣ሙሽሪኮቹ ሊገድሏቸው እያሳደዷቸው፣አብሯቸው ዋሻው ውስጥ ለሚገኙት ባልደረባቸው ለአቡበክር (ረ.ዐ.) የተናገሩትን በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{لَا تَحْزَنْ إِنَّ ٱللَّهَ مَعَنَا ۖ فَأَنزَلَ ٱللَّهُ سَكِينَتَهُۥ عَلَيْهِ وَأَيَّدَهُۥ بِجُنُودٍ لَّمْ تَرَوْهَا وَجَعَلَ كَلِمَةَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ ٱلسُّفْلَىٰ ۗ وَكَلِمَةُ ٱللَّهِ هِىَ ٱلْعُلْيَا ۗ وَٱللَّهُ عَزِيزٌ حَكِيمٌ ﴿٤٠﴾} [التوبة: ٤٠]

‹‹አትዘን፣አላህ ከእኛ ጋር ነውና ባለ ጊዜ፣አላህ እርካታውን በርሱ ላይ አወረደ፤ባላያችኋቸውም ሰራዊት አበረታው፤የነዚያንም የካዱትን ሰዎች ቃል ዝቅተኛ አደረገ፤የአላህም ቃል እርሷ ከፍተኛ ናት፤አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው፡፡››[አል ተውበህ:40]



አማኝ ሰው የሞት ቀጠሮና ውሳኔው በአላህ (ሱ.ወ.) እጅ ብቻ መሆኑን በእርግጠኝነት ስለሚያውቅ ሞትን አይፈራም፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ٱللَّهُ يَتَوَفَّى ٱلْأَنفُسَ حِينَ مَوْتِهَا وَٱلَّتِى لَمْ تَمُتْ فِى مَنَامِهَا ۖ فَيُمْسِكُ ٱلَّتِى قَضَىٰ عَلَيْهَا ٱلْمَوْتَ وَيُرْسِلُ ٱلْأُخْرَىٰٓ إِلَىٰٓ أَجَلٍ مُّسَمًّى ۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَٰتٍ لِّقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ ﴿٤٢﴾} [الزمر: ٤٢]

‹‹አላህ ነፍሶችን በሞታቸው ጊዜ ይወስዳል፤ያችንም ያልሞተችውን በእንቅልፏ ጊዜ፣(ይወስዳታል)፤ታዲያ ያችን ሞትን የፈረደባትን ይይዛታል፤ሌላይቱንም እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ይለቃታል፤በዚህ ውስጥ ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች ምልክቶች አሉበት፡፡››[አል ዙመር:42]

ሙእምን ሰው፣ሞት ፈጽሞ ሊሸሹት የማይቻልና የማይቀር እውነታ መሆኑንም በእርግጠኝነት ያውቃል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦


{قُلْ إِنَّ ٱلْمَوْتَ ٱلَّذِى تَفِرُّونَ مِنْهُ فَإِنَّهُۥ مُلَٰقِيكُمْ ۖ ثُمَّ تُرَدُّونَ إِلَىٰ عَٰلِمِ ٱلْغَيْبِ وَٱلشَّهَٰدَةِ فَيُنَبِّئُكُم بِمَا كُنتُمْ تَعْمَلُونَ ﴿٨﴾} [الجمعة: ٨]


‹‹ያ ከርሱ ምትሸሹት ሞት፣እርሱ በእርግጥ አግኛችሁ ነው፤ከዚያም ሩቁንና ቅርቡን ዐዋቂ ወደኾነው (ጌታ) ትመለሳላችሁ፤ትሠሩትም የነበራችሁትን ሁሉ ይነግራችኋል በላቸው፡፡ ››[አል ጁሙዓ:8]

ሞት ተወስኖ በተጻፈለት ቀነቀጠሮ እንጂ የማይመጣ መሆኑንም ይረዳል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَوْ يُؤَاخِذُ ٱللَّهُ ٱلنَّاسَ بِظُلْمِهِم مَّا تَرَكَ عَلَيْهَا مِن دَآبَّةٍ وَلَٰكِن يُؤَخِّرُهُمْ إِلَىٰٓ أَجَلٍ مُّسَمًّى ۖ فَإِذَا جَآءَ أَجَلُهُمْ لَا يَسْتَـْٔخِرُونَ سَاعَةً ۖ وَلَا يَسْتَقْدِمُونَ ﴿٦١﴾} [النحل: ٦١]

‹‹አላህም ሰዎችን በበደላቸው በያዛቸው ኖሮ፣በርሷ (በምድር) ላይ ከተንቀሳቃሽ ምንም ባልተወ ነበር፤ግን እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ያቆያቸዋል፤ጊዜያቸውም በመጣ ወቅት፣አንዲትን ሰዓት አይቆዩም፤አይቀደሙምም፡፡››[አል ነሕል:61]





## እምነት . . እና ሕይወት

‹‹እምነት የሰውን ኑሮ ለማገዝ የግድ መኖር ካለባቸው ኃይሎች አንደኛው ነው፡፡ እርሱን ማጣት ደግሞ የሕይወትን ጣጣዎች ለመጋፈጥ ድክመት መኖሩን ማስጠንቀቂያ ነው፡፡››

**አርነስት ሬይኔህ**
**ፈረንሳዊ ታሪክ ጸሐፊ**



https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am


## ቁሳዊ ሥልጣኔዎች ይውደሙ



‹‹እስላም በመርሆዎቹ መረጋጋትን ነፍስ ውስጥ እንደሚዘራ አረጋግጫለሁ:: ቁሳዊ ስልጣኔ ግን በምንም ነገር ስለማያምኑ ባለቤቶቹን ወደ ቀቢጠ ተስፋ ይመራቸዋል:: በራሳቸው ቁሳዊ መመዘናዎች ስለሚመዝኑት፣አውሮፓውያን የእስላምን እውነታ እንዳልተረዱም አረጋግጫለሁ::››

ሮዤህ ዶባኬይ

ስዊዘርላንዳዊ አሳቢና ጋዜጠኛ



https://www.path-2-happiness.com/am

## 7- ወዶ መቀበልና በተሰጡት መርካት (ሪዷ) የደስተኝነት መግቢያ በር ነው፦

ደስተኝነት አላህ (ሱ.ወ.) የሰጠውን ወዶ መቀበልና ባለው መርካት ነው:: መብሰልሰል፣መቆጨትና መከፋት ግን የሰውን ሕይወት፣መንፈሱንና ስሜቱን የሚበክል መርዝ ነው:: በተሰጡት ዕጣ ፈንታ ረክቶ የአላህን ውሳኔና እርሱ የመረጠውን ወዶ መቀበል (ሪዷ) የደስተኝነት፣የእርካታ፣የእፎይታና የመታደል መግቢያ በር ነው:: ይህ እርካታ የሰው ልጅ የሚያጋጥመውን ሁሉ በጎ፣አስደሳች፣ገንቢና ጠቃሚ እንዲሆን ያደርጋል:: ይህ ሲሆንም ነፍሱ ከፈጣሪ ጌታዋ በስተቀር ከሌላ ምንም አትከጅልም፤ባመለጣት ዓለማዊ ደስታም አትቆጭም:: በአላህ ውሳኔ ረክቶ ጥረትና ትጋቱን እየቀጠለ መልካሙን ሁሉ ከጌታው ይለምናል:: ሪዷ የተለያዩ መልኮች ያሉት ሲሆን፣አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው፦

ሀ) አላህን በጌትነት፣እስላምን በሃይማኖትነት፣ሙሐመድን ﷺ በነቢይነትና በመልክተኛነት ወዶና ረክቶ መቀበል አንዱ ነው:: ይህን ወዶና ረክቶበት ያልተቀበለ ሰው፣በማያቋርጥ ጭንቀትና የግራመጋባት ሁኔታ ውስጥ ይኖራል:: ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹አላህን በጌትነት፣እስላምን በሃይኖትነት፣ሙሐመድን ﷺ በመልክተኛነት ወዶና ረክቶ የተቀበለ ሰው የኢማንን ጣዕም ቀምሷል::›› [በቡኻሪ የተዘገበ] የኢማንን ጥፍጥና ያልቀመሰ ሰውም የደስተኝነትን ጣዕም አልቀመሰም፤ሕይወቱ የመከፋትና የጭንቀት ሕይወት እንደሆነ ይቀጥላል:: የአላህን ጌትነት ወዶ መቀበል ማለት በአላህ (ሱ.ወ.) መኖር ማመን፣የፈጣሪ አምላክን ኃያልነት፣ጥበቡን፣ ችሎታውን፣ፍጹማዊ ዕውቀቱን፣መልካሞቹን ስሞቹን ማወቅ ማለት ነው:: በርሱ ማመንን፣አምልኮቱንና ለርሱ ብቻ ተገዥ መሆንን በእርካታ መቀበል ማለት ነው:: ይህን ያላደረገ ሰው፣አላህ ይጠብቀንና በጥርጣሬና በግራ መጋባት፣ በሕመምና በጭንቀት ውስጥ የሚኖር ነው::

ለ) የአላህን ፍርድና ሸሪዓውን በእርካታ ወዶ መቀበል ሌላው የሪዷ ገጽታ ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{فَلَا وَرَبِّكَ لَا يُؤْمِنُونَ حَتَّىٰ يُحَكِّمُوكَ فِيمَا شَجَرَ بَيْنَهُمْ ثُمَّ لَا يَجِدُوا فِي أَنفُسِهِمْ حَرَجًا مِّمَّا قَضَيْتَ وَيُسَلِّمُوا تَسْلِيمًا ﴿٦٥﴾} [النساء: ٦٥]

‹‹በጌታህም እምላለሁ (አላህ በራሱ መማሉ ነው)፣በመካከላቸው በተከራከሩበት ፍርድ እስከሚያስፈርዱህ፣ከዚያም ከፈረድከው ነገር በነፍሶቻቸው ውስጥ ጭንቀትን እስከማያገኙና ፍጹም መታዘዝን እስከሚታዘዙ ድረስ አያምኑም (ምእመን አይኾኑም)::››[አልኒሳእ:65]

የሰው ልጆች፣የሚበጃቸውን ሁሉ የሚያውቀው ፈጣሪያቸውን ሕግጋት ትተው ሰው ሠራሽ በሆኑ ጎጂና ጎደሎ ሕግጋትና ሥርዓቶች በመተዳደራቸው፣ብዙ አስከፊ ችግሮችንና የሕይወት ፈተናዎችን ለመጋፈጥ፣ስቃይ አበሳቸውንም ለመጋት ተገደዋል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{أَلَا يَعْلَمُ مَنْ خَلَقَ وَهُوَ اللَّطِيفُ الْخَبِيرُ ﴿١٤﴾} [الملك: ١٤]


‹‹የፈጠረ አምላክ እርሱ ዕውቀተ ረቂቁ፣ውስጥ ዐዋቂው ሲኾን (ምስጢርን ሁሉ) አያውቅምን?)››[አል ሙልክ:14]

ሐ) የአላህን (ሱ.ወ.) ፍርድና ቅድመ ውሳኔውን ወዶ በእርካታ መቀበልም ሌላው የሪዷ ገጽታ ነው:: እናም ሙስሊም ሰው ከአላህ (ሱ.ወ.) መሻትና ቅድመ ውሳኔ ውጭ ምንም ነገር እንደማያገኘውና እርሱ ልቡን እንደሚመራው በውስጡ እርግጠኝነትን ስለሚያሳድር የአላህን ቀዷእና ቀደር በጸጋና በውዴታ ይቀበላል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{مَا أَصَابَ مِن مُّصِيبَةٍ إِلَّا بِإِذْنِ اللَّهِ ۗ وَمَن يُؤْمِن بِاللَّهِ يَهْدِ قَلْبَهُ ۚ وَاللَّهُ بِكُلِّ شَيْءٍ عَلِيمٌ ﴿١١﴾} [التغابن: ١١]

‹‹ከመከራም (ማንንም) አይነካም፣በአላህ ፈቃድ ቢኾን እንጅ፤በአላህም የሚያምን ሰው፣ልቡን (ለትዕግስት) ይመራዋል፤አላህም ነገሩን ሁሉ ዐዋቂ ነው::››[አል ተጋቡን:11]

ሙስሊሙ ችግርና መከራን ከአላህ በስተቀር ማስወገድ የሚችል አለመኖሩን በእርግጠኝነት ስለሚያውቅ የአላህን ቀዷእና ቀደር (ሁሉም ነገር




በርሱ ዕውቀት፣በርሱ መሻትና ቅድመ ውሳኔ ብቻ የሚፈጸም መሆኑን) በጸጋና በእርካታ ይቀበላል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِن يَمْسَسْكَ ٱللَّهُ بِضُرٍّ فَلَا كَاشِفَ لَهُۥٓ إِلَّا هُوَ ۖ وَإِن يُرِدْكَ بِخَيْرٍ فَلَا رَآدَّ لِفَضْلِهِۦ ۚ يُصِيبُ بِهِۦ مَن يَشَآءُ مِنْ عِبَادِهِۦ ۚ وَهُوَ ٱلْغَفُورُ ٱلرَّحِيمُ ﴿١٠٧﴾} [يونس: ١٠٧]

‹‹አላህም ጉዳትን ቢያደርስብህ፣ከርሱ ሌላ ለርሱ ገላጭ የለውም፤በጎንም ነገር ቢሻልህ፣ለችሮታው መላሽ የለም፤ከባሮቹ የሚሻውን በርሱ ይለይበታል፤እርሱም መሓሪ አዛኝ ነው፡፡››[ዩኑስ፡107]

በጣም አስደናቂው ነገር፣እምነት አማኙ ከአላህ (ሱ.ወ.) የተወሰነለትን ዕጣ ፈንታ ወዶ በእርካታ እንዲቀበል፣ችግርና መከራን በትዕግስት እንዲያሳልፍ፣የአላህን (ሱ.ወ.) ጸጋና ቸርነቱን እንዲያመሰግን የሚያደርገው መሆኑ ነው፡፡ ይህን ውስጣዊ እርካታ ማግኘት የሚችሉት ምእመናን ብቻ ናቸው፡፡ ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ሙእምን ሰው ነገሩ ሁሉ አስደናቂ ነው፡፡ የርሱ ነገር ሁሉ ለበጎ ነው፤ይህ ለማንም ሳይሆን ለአማኝ ሰው ብቻ የሚሆን ነው፡፡ አስደሳች ነገር ሲያጋጥመው ያመሰግናል፣በጎም ይሆንለታል፡፡ ክፉ ነገር ቢያጋጥመውም ይታገሳል፣በጎም ይሆንለታል፡፡››[በሙስሊም የተዘገበ] ሌላው ቀርቶ በዓለማዊ ጸጋና ሀብት ከኛ በላይ የሆኑትን ስናይ በተሰጠን እንዴት እንደምንረካም ነቢዩ ﷺ ሲያስተምሩን እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹አላህ የዋለላችሁን ጸጋ እንዳትንቁ ለማድረግ ይበልጥ የተገባ ነውና፣(በቁሳዊ ሀብት) ከናንተ በታች የሆኑትን ተመልከቱ እንጂ ከናንተ በላይ የሆኑትን አትመልከቱ፡፡›› [በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ]



ሬክስ እንግራም
ዓለም አቀፍ ታዋቂነት ያለው የፊልም ፕሮዲዩሰር

### የእስላም መንፈስ

‹‹እስላም መረጋጋትና ሰላምን ለነፍስ የሚሰጥ፣ለሰው ልጅ በዚህ ዓለም ሕይወቱ መጽናናትን፣የሕሊና እፎይታንና እርካታን እንዲሰነቅ የሚያደርግ ሃይማኖት ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ የእስላም መንፈስ ወደ ነፍሴ ሰርጾ ገብቶ በመለኮታዊው ውሳኔ የማመን ጸጋ እንዲሰማኝ፣ለአስደሳችም ሆኑ ለአሳማሚ ቁሳዊ ተጽእኖዎች ግድ የሌሽ የመሆን ስሜትም እንዲያድርብኝ ማድረግ ችሏል፡፡››



## ከደስተኝነት መንገድ የመራቅ ስቃይና ዕድለ ቢስነት፦

እስላም ለሁሉም ጊዜና ቦታ ምቹ፣ከሰው ልጆች ተፈጥሮ ጋር የሚጣጣም፣የሕይወትን ተለዋዋጭ ሁኔታዎች ግንዛቤ ውስጥ የሚያስገባ፣ከሰው ልጅ ሥልጣኔና ዕድገት ጋር የሚራመድ፣ለዓለም ሕዝቦች ኢኮኖሚያዊ፣ፖለቲካዊ፣ማሕበራዊና ሌሎችም ችግሮች መፍትሔ ሰጭ ሆኖ ነው ከአላህ (ሱ.ወ.) የተላለፈው፡፡ ይሁን እንጂ በዙ ሰዎች ከዚህ ብሩህ ጎዳና ሲያፈነግጡ፣ሌሎች ደግሞ ሰዎችን ከርሱ ለማራቅ ገጽታውን የማበላሸት ጦርነት ከፍተውበታል፡፡ ይህም ብዙውን የዓለም ሕዝብ ለከፋ ችግር አጋልጧል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) መመሪያውን ለተከተለና በሕጎቹ ለተመራ ሁሉ በዛሬዋ ዓለም ሕይወቱና በወዲያኛው ዓለም ደስተኝነትንና መታደልን ሊያጎናጽፈው ዋስትና ሲሰጥ፣ከርሱ ባፈነገጠና በተኩራራ ላይ ደግሞ ውርደትንና ዕድለ ቢስነትን ወስኖበታል፡፡

አላህ (ሱ.ወ.) ይህን እስላም ለሰው ልጆች የሰጠው ሕይወታቸው የተስተካከለ፣ኑሯቸውም ያማረ፣በዛሬው የመጀመሪያ ሕይወታቸውም ሆነ በመጪው ዘላለማዊ ሕይወታቸው መታደልን እንዲያገኙና ከመከራም ይድኑ ዘንድ ነው፡፡ የሰው ልጅ ነፍስ ግን በተፈጥሯ ስሜታዊ ዝንባሌዎቿንና ሥጋዊ ፍላጎቶቿን የሚገድቡ ግዴታዎችን - ግዴታዎቹ ለራሷ የሚበጁ ቢሆኑ እንኳ - አትፈልግም፡፡ በዚህም ምክንያት እውነታን የሚያውቁ ደጋግ ሰዎች እነሱ ወደ ደረሱበት እውነትና ቅን መንገድ ይመጡ ዘንድ ሰዎችን ወደ እውነትና ወደ በጎ ነገር የመጥራትና የማስተማር (የደዕዋ) ግዴታ አላህ (ሱ.ወ.) ጥሎባቸዋል፡፡ ደዕዋውንም ለዓለማት ሁሉ እንዲያደርሱ አዟቸዋል፡፡ የአላህ መልክተኛም ﷺ የተላኩት ለመታደልና ከርሳቸው ጋር ያሉት፣ሕዝባቸውና መላው የሰው ዘርም አብሯቸው እንዲታደል ለማድረግ ዓለማ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{مَآ أَنزَلْنَا عَلَيْكَ ٱلْقُرْءَانَ لِتَشْقَىٰٓ ﴿٢﴾} [طه: ٢]

‹‹ቁርኣንን፣ባንተ ላይ እንድትቸገር አላወረድንም፡፡››[ጣሃ፡2]





https://www.path-2-happiness.com/am

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَآ أَرۡسَلۡنَٰكَ إِلَّا رَحۡمَةٗ لِّلۡعَٰلَمِينَ ۝١٠٧}[الأنبياء: ١٠٧]

‹‹(ሙሐመድ ሆይ!) ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጅ አልላክንህም::››[አል አንቢያ፡ 107]

በመሆኑም ነቢዩን ﷺ መከተል፣በፈለጋቸው መጓዝ፣መንገዳቸውን አጥብቆ መያዝ የደስተኝነትና የመታደል ምንጭ ነው:: የመድህን ዋስትና ነው:: ትእዛዛቱን በመፈጸምና ከእገዳዎቹ በመራቅ ክልል ውስጥ አላህ (ሱ.ወ.) እንድንመራው ያዘዘን የአነዋነዋር መንገድ ነው:: ውጤቱም የዛሬውና የነገው ሕይወት ተድላና ደስታ ብቻ ነው:: ከዚህ ነቢያዊ ፈለግ ማፈንገጥ ግን ውጤቱ የዛሬውና የነገው ዘላለማዊ ሕይወት ውድቀትና ዕድለ ቢስነት ብቻ ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَنۡ أَعۡرَضَ عَن ذِكۡرِي فَإِنَّ لَهُۥ مَعِيشَةٗ ضَنكٗا وَنَحۡشُرُهُۥ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ أَعۡمَىٰ ۝١٢٤ قَالَ رَبِّ لِمَ حَشَرۡتَنِيٓ أَعۡمَىٰ وَقَدۡ كُنتُ بَصِيرٗا ۝١٢٥ قَالَ كَذَٰلِكَ أَتَتۡكَ ءَايَٰتُنَا فَنَسِيتَهَاۖ وَكَذَٰلِكَ ٱلۡيَوۡمَ تُنسَىٰ ۝١٢٦} [طه: ١٢٤-١٢٦]

‹‹ከግሣጼየም የዞረ ሰው፣ለርሱ ጠባብ ኑሮ አልለው፤በትንሣኤም ቀን ዕውር ኾኖ እንቀሰቅሰዋለን:: ፦ ጌታዬ ሆይ! ለምን ዕውር አድርገህ አስነሳኸኝ? በእርግጥ የማይ የነበርኩ ስኾን ይላል:: (ነገሩ) እንደዚሁ ነው፤ታምራታችን መጣችልህ፤ተውካትም፤እንደዚሁም ዛሬ ትትተዋለህ፤ይለዋል::›› [ጣሃ፡124-126]



### ኀሐ እስላም

‹‹ታሪክ በጥቅሉ ወደርሱ ያነጣጠረ የሚመስለው ታላቁ የእስላም አዲስ ኀሕ ከመቅደዱ በፊት ስንት ትውልዶች በፍርሃትና በዕድለ ቢስነት ይጠቁ ይሆን! በዚያን ቀን ሰላም ምድሪቱን ያጥለቀልቃል:: በዚያም ቀን ሰላም ልቦችን ያጥለቀልቃል::››

ሀርበርት ጆርጅ ዌልዝ

እንግሊዛዊ ጸሐፊና የስነጽሑፍ ምሁር

አላህ (ሱ.ወ.)፦

{فَلَنُحۡيِيَنَّهُۥ حَيَوٰةٗ طَيِّبَةٗ} [النحل: ٩٧]

‹‹መልካም ኑሮን በእርግጥ እናኖረዋለን፤››[አል ነሕል፡97]

በማለት በገለጸው አማኝና ቀጥሎ በተገለጸው ከአላህ ውዳሴ ፊቱን ባዞረው ሰው መካከል ያለው ልዩነትም የሰፋ ነው፦

{فَإِنَّ لَهُۥ مَعِيشَةٗ ضَنكٗا}[طه: ١٢٤]

‹‹ለርሱ ጠባብ ኑሮ አልለው፤›› [ጣሃ፡124]



መልካም ሕይወትን መታደል የሚቻለው፣በግልጽና በስውርም የአላህን ትእዛዛት በመፈጸምና ከእገዳዎቹ በመራቅ፣የምንኖረው በርሱ ጥበቃና እንክብካቤ ስር በመሆኑ የአላህን (ሱ.ወ.) ውሳኔ በጸጋና በእርካታ በመቀበል ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَتَطۡمَئِنُّ قُلُوبُهُم بِذِكۡرِ ٱللَّهِۗ أَلَا بِذِكۡرِ ٱللَّهِ تَطۡمَئِنُّ ٱلۡقُلُوبُ ۝٢٨}[الرعد: ٢٨]

‹‹(እነሱም) እነዚያ ያመኑ፣ልቦቻቸውም አላህን በማውሳት የሚረኩ ናቸው፤ንቁ አላህን በማውሳት ልቦች ይረካሉ::››[አል ረዕድ፡28]

የልቦና መረጋጋትና ውስጣዊ እርካታ የሰው ልጅ በሚፈጽማቸው ተግባራት ሁሉ ይንጸባረቃል:: በተቃራኒው ጭንቀትና ውስጣዊ ውጥረትም ውጡቱ አስከፊ ይሆናል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَن يُرِدۡ أَن يُضِلَّهُۥ يَجۡعَلۡ صَدۡرَهُۥ ضَيِّقًا حَرَجٗا كَأَنَّمَا يَصَّعَّدُ فِي ٱلسَّمَآءِۚ كَذَٰلِكَ يَجۡعَلُ ٱللَّهُ ٱلرِّجۡسَ عَلَى ٱلَّذِينَ لَا يُؤۡمِنُونَ ۝١٢٥}[الأنعام: ١٢٥]

‹‹ሊያጠመውም የሚሻውን ሰው፣ደረቱን ጠባብ፣ቸጋራ፣ወደ ሰማይ ለመውጣት እንደሚታገል፣ያደርገዋል:: እንደዚሁ አላህ በነዚያ በማያምኑት ላይ ርክሰትን ያደርጋል::››[አል አንዓም፡ 125]

ጥበቱ፣ቸጋራነቱና አስከፊ ኑሮው በድህነትና በበሽታ ምክንያት የመጣ ሳይሆን፣በሁሉም ተግባሩ ወይም በሁሉም ነገሩ ውስጥ ከሚንጸባረቀው ውስጣዊ ውጥረትና አለመረጋጋት ሁኔታ የሚመነጭ ነው:: ያልታደለን ሰው ሀብት ማግኘትም ሆነ ማጣት ከዚህ ክልል አያስወጣውም፤የአለመታደሉ መንስኤ ይህ አይደለምና:: መንስኤው አመለካከትና የእሳቤ መንገዱ ነው:: የሀብቱ መጨመር ወይም መቀነስ፣መታመሙ ወይም ጤነኛ መሆኑ ጭንቀትና አለመታደሉ እንዲባባስ ምክንያት ሊሆንም ይችላል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦





https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

{فَلَا تُعۡجِبۡكَ أَمۡوَٰلُهُمۡ وَلَآ أَوۡلَٰدُهُمۡۚ إِنَّمَا يُرِيدُ ٱللَّهُ لِيُعَذِّبَهُم بِهَا فِي ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا وَتَزۡهَقَ أَنفُسُهُمۡ وَهُمۡ كَٰفِرُونَ ﴿٥٥﴾} [التوبة: ٥٥]

‹‹ገንዘቦቻቸውና ልጆቻቸውም አይድነቁህ፤አላህ የሚሻው በቅርቢቱ ሕይወት በነርሱ (በገንዘቦቻቸውና በልጆቻቸው) ሊቀጣቸው፣ነፍሶቻቸውም እነሱ ከሓዲዎች ኾነው ነፍሶቻቸው እንዲወጡ ብቻ ነው፡፡››[አል ተውበህ፡ 55]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَا تُعۡجِبۡكَ أَمۡوَٰلُهُمۡ وَأَوۡلَٰدُهُمۡۚ إِنَّمَا يُرِيدُ ٱللَّهُ أَن يُعَذِّبَهُم بِهَا فِي ٱلدُّنۡيَا وَتَزۡهَقَ أَنفُسُهُمۡ وَهُمۡ كَٰفِرُونَ ﴿٨٥﴾}[التوبة: ٨٥]

‹‹ገንዘቦቻችውና ልጆቻቸውም አይድነቁህ፤አላህ የሚሻው፣በቅርቢቱ ዓለም በነሱ ሊቀጣቸውና፣ከሓዲዎችም ኾነው ነፍሶቻቸው እንዲወጡ ብቻ ነው፡፡››[አል ተውበህ፡ 85]

የሰው ልጆችን በተመለከተ አለመታደልና ደስተኝነትን ማጣት ሀብታም ወይም ደሃ ከመሆን ጋር አይያያዝም፡፡ ከበሽታ ወይም ከፈታኝ ነገር ጋርም አይገናኝም፡፡ አለመታደል ማለት ከአላህ (ሱ.ወ.) መራቅ፣ከርሱ መንገድ ማፈንገጥ፣ከፈጣሪ ጌታ ጋር ግንኙነት አልባ መሆን ነው፡፡ ዘከሪያ ﷺ በጸሎታቸው አላህን (ሱ.ወ.) ሲማጸኑ እንዲህ ብለዋል፦

{وَلَمۡ أَكُنۢ بِدُعَآئِكَ رَبِّ شَقِيّٗا ﴿٤﴾} [مريم: ٤]

‹‹አንተንም በመለመኔ ጌታዬ ሆይ! (ምንጊዜም) ዕድለ ቢስ አልኾንም፡፡››[መርየም፡4]


ባለፉት ጊዜያት ለጸሎቴ ምላሽ በመስጠትና ልመናዬን በመቀበል አክብረኸኛል፤አሁንም ልመናዬን በመስማት ዕድለኛ አድርገኝ፣ነበር ያሉት፡፡ ይህ በዘከሪያ ላይ ብቻ የሚወሰን አይደለም፡፡ ጌታችን አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሎናልና፦

{وَإِذَا سَأَلَكَ عِبَادِي عَنِّي فَإِنِّي قَرِيبٌۖ أُجِيبُ دَعۡوَةَ ٱلدَّاعِ إِذَا دَعَانِۖ فَلۡيَسۡتَجِيبُواْ لِي وَلۡيُؤۡمِنُواْ بِي لَعَلَّهُمۡ يَرۡشُدُونَ ﴿١٨٦﴾} [البقرة: ﴿١٨٦﴾]

‹‹ባሮቼ ስለኔ በጠየቁህ ጊዜ፣እኔ ቅርብ ነኝ፤የለማኙን ጸሎት በለመነኝ ጊዜ፣እቀበለዋለሁ፤ስለዚህም ወደ ቅኑ መንገድ ይመሩ ዘንድ በኔ ይመኑ፡፡››[አል በቀራህ፡186]

በአገልጋይ ባሪያውና በፈጣሪ አምላኩ መካከል ቀጥተኛ





ግንኙነትና ትስስሩ እስካለ ድረስ፣መታደልን የማግኘት ዕድል የተረጋገጠ ነው፡፡ ዕድለ ቢስነት የሚያጋጥመው ይህ ትስስር ሲቋረጥ ነው፡፡ አንድ ሰው ራሱን ለዚህ ሃይማኖት ተገዥ ማድረጉን በአኻደለ መጠን በራሱና በሕይወቱ ላይ እንከንና አለመረጋጋት ይፈጠራል፡፡

ለዚህ ነው አላህ (ሱ.ወ.) ቅን መመሪያን ከእዝነትና ከጸጋው ጋር፣ጥመትን ደግሞ ከዕድለ ቢስነት ጋር የሚያስተሳስረው፡፡ የመጀመሪያውን አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{أُوْلَٰٓئِكَ عَلَىٰ هُدٗى مِّن رَّبِّهِمۡۖ وَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡمُفۡلِحُونَ ﴿٥﴾}[البقرة: ٥]

‹‹እነዚያ ከጌታቸው በመመራት ላይ ላይ ናቸው፤እነዚያም እነርሱ ፍላጎታቸውን ያገኙ ናቸው፡፡››[አል በቀራህ፡5]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{أُوْلَٰٓئِكَ عَلَيۡهِمۡ صَلَوَٰتٞ مِّن رَّبِّهِمۡ وَرَحۡمَةٞۖ وَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡمُهۡتَدُونَ ﴿١٥٧﴾} [البقرة: ١٥٧]

‹‹እነዚያ ከጌታቸው የኾኑ ምሕረቶችንና ችሮታንም የሚቀበሉ ናቸው፤እነርሱም የተመሩት እነርሱ ናቸው፡፡››[አል በቀራህ፡157]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{فَإِمَّا يَأۡتِيَنَّكُم مِّنِّي هُدٗى فَمَنِ ٱتَّبَعَ هُدَايَ فَلَا يَضِلُّ وَلَا يَشۡقَىٰ ﴿١٢٣﴾}[طه: ١٢٣]

‹‹ከኔም የኾነ መሪ ቢመጣላችሁ፣መሪየን የተከተለ፣ አይሳሳትም፤ አይቸገርምም፡፡››[ጣሃ፡123]

ከርሱ ዘንድ የሆነ መመሪያ (አልሁዳ) ከጥመት ማዳኑ ሲሆን፣እዝነት (ረሕመት) ደግሞ ከዕድለ ቢስነት መታደጉ ነው፡፡ በጣሃ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ ያወሳው እውነታም ይኸው ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{طه ﴿١﴾ مَآ أَنزَلۡنَا عَلَيۡكَ ٱلۡقُرۡءَانَ لِتَشۡقَىٰٓ ﴿٢﴾}[طه: ١-٢]

‹‹ጠ.ሀ. (ጣሃ) [አንተ ሰው] ቁርኣንን፣ባንተ ላይ እንድትቸገር አላወረድንም፡፡››[ጣሃ፡1-2]

ከላይ ቁርኣንን በነቢዩ ﷺ ላይ ማውረድንና ዕድለ ቢስነትን ከርሳቸው ማራቅን ሲያጣምር፣በምዕራፉ መጨረሻ ላይ ደግሞ ተከታዮቻቸውን አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{فَلَا يَضِلُّ وَلَا يَشۡقَىٰ ﴿١٢٣﴾} [طه: ١٢٣]

‹‹አይሳሳትም፤አይቸገርምም፡፡››[ጣሃ፡123]

ወደ ቅኑ መንገድ መመራት፣ችሮታ፣ጸጋና እዝነት



https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

እርስ በርሳቸው የተያያዙና የማይነጣጠሉ ሲሆኑ፤ ጥመትና አለመታደልም እንደዚሁ የተያያዙና የማይነጣጠሉ ናቸው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّ ٱلۡمُجۡرِمِينَ فِي ضَلَٰلٖ وَسُعُرٖ ٤٧} [القمر: ٤٧]


‹‹አመጠኞች በስሕተትና በእሳቶች ውስጥ ናቸው።››[አል ቀመር፡47]

ከመንገዱ ያፈነገጡ አመጸኞች መጨረሻ አስከፊውና መራሩ የገሀነም እሳት ነው። በአንጻሩ ደግሞ አላህን (ሱ.ወ.) የሚፈሩ ትጉህ ታዛዥ አገልጋዮቹ መጨረሻን አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ.) በዚሁ ተመሳሳይ ምዕራፍ ውስጥ እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّ ٱلۡمُتَّقِينَ فِي جَنَّٰتٖ وَنَهَرٖ ٥٤ فِي مَقۡعَدِ صِدۡقٍ عِندَ مَلِيكٖ مُّقۡتَدِرِۭ ٥٥} [القمر: ٥٤-٥٥]

‹‹አላህን ፈሪዎቹ በአትክልቶችና በወንዞች ውስጥ ናቸው። (እነሱም ውድቅ ቃልና መውወንጀል በሌለበት) በውነት መቀመጫ ውስጥ፣ቻይ እኾነው ንጉሥ ዘንድ ናቸው።››[አል ቀመር፡ 54-55]

ማግኘት ለሚፈልግ ሰው የደስተኝነት መንገድና የመታደል ጎዳናው ይህ ነው። መንገዱን ከተያያዝከው በአፈታሪኮች በመንፈሳዊም





ሆነ ርእዮታዊ ባዶ መናፌቅነት ላይ ያልተመሰረተ መንገድ ነው። የደስተኝነት መንገድ፣የመታደል ጎዳና ነው። በተጨማሪም የዕውቀትና የሥልጣኔ መንገድ ነው።

### የሰው ልጆች አዳኝ

‹‹ሙሐመድን ‹የሰው ልጆች አዳኝ› ብሎ መሰየም ፍትሐዊነት ነው። እርሱን የመሰለ ሰው የአዲሱን ዓለም መሪነት ቢሾም ለችግሮቹ መፍትሔ ለማግኘት ስኬታማ በሆነና ደስተኝነትና ሰላምን ባስገኘለት ነበር፣የሚል እምነት አለኝ።

በርናርድ ሾው

እንግሊዛዊ ጸሐፊ

